# በአብክመ
# የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ

## ከ2018–2022 የ5 ዓመት ዕቅድ

ሚያዝያ 2016 ዓ.ም

ባህርዳር

## Contents


1. መግቢያ ...... 3

2. የሁኔታ ትንተና ...... 5

2.1 ሀገራዊና ክልላዊ ሁኔታ ትንተና ...... 5

2.2 ተቋማዊ ዳሰሳ /ትንተና ...... 6

2.2.1 ውስጣዊ ሁኔታዎች (ጥንካሬና ድክመት) ...... 7

2.3. ስትራቴጅክ ጉዳዮች ትንተና ...... 9

2.3.1 የሰው ኃይል ልማት ...... 9

2.3.2 የመስኖ ቴክኖልጂ ...... 10

2.3.3 የመስኖ ምርምር ...... 11

2.3.4 የመስኖ መሰረተ ልማት ...... 12

2.3.5 የመስኖ ስራ አደረጃጀት ...... 12

2.3.6 የመስኖ ቁሳቁሶችንና መሳሪያዎችን ማምረት ...... **Error! Bookmark not defined.**

3. ርዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች ...... 13

ራዕይ ...... 13

ተልዕኮ ...... 13

እሴቶች ...... 13

4. የዕቅዱ መነሻዎች ...... 14

4.1 ያለፉት በጀት ዓመታት አፈፃፀም እንደ መነሻ ...... 14

4.1.1 ከቁልፍ ተግባር አኳያ ሴክተሩ ያለበት ሁኔታ ...... 14

4.1.2 የአበይት ተግባራት አፈጻፀም ...... 21

4.2 በአገር አቀፍ ደረጃ የመስኖ ሴክተር ዕቅድ እንደ መነሻ ...... 22

4.3 በአለም አቀፍ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የዘላቂ ልማት ግቦች እንደ መነሻ ...... 23

4.3.1 የዘላቂ ልማት ግቦች ...... 23

4.3.2 የአጀንዳ 2063 ግቦች ...... 24

4.4 ሀገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች እንደ መነሻ ...... 24

4.4.1 የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች: ...... 24

4.4.2 የማስፈጸም አቅም ግንባታ ስትራቴጂና ፕሮግራሞች፤ ...... 24

4.4.3 የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ፤ ...... 25

4.4.4 የመስኖ ጥናትና ዲዛይን እና ግንባታ ህጎች፤ ......25

4.4.5 የግዥ አፈጻጸምና የንብረት አስተዳደር መመሪያዎች፤ ......25

4.5 አገራዊና ክልላዊ ራዕይ እንደመነሻ ......26

**4.6 ለዘርፉ ወሳኝ የሆኑ ሀብቶች እንደመነሻ ......27**

ሀ.የዉሃ ሀብት......27

ለ. በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት ......27

ሐ. የተቋሙ የቴክኖሎጅ አቅም......28

መ. የሰው ሀብት......29

**5. የትኩረት መስኮች ......29**

**6. የዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች......30**

**7. የቢሮው የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ ......31**

7.1 የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ጥቅል ዓላማ፡ ......31

7.2 የቢሮው ግቦችና......31

**8. የማስፈጸሚያ ስልቶች ......**Error! Bookmark not defined.

**9. የዕቅዱ ማስፈፀሚያ ሀብት......32**

**10. ስጋቶችና እሳቤዎች ......35**

ሀ. መልካም አጋጣሚ (እሳቤዎች)......35

ለ. ስጋቶች......35

**11. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ......37**

**12. የድርጊት መርሀ-ግብር ......38**

## 1. መግቢያ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በ8º 45’ እስከ 13º 45’ ሰሜን የኬክሮስ እና በ35º 46’ እስከ 40º25’ ምሥራቅ የኬንትሮስ መስመር ውስጥ ይገኛል፡፡ በሰሜን ከትግራይ፣ በምሥራቅ ከአፋር፣ በደቡብ ከኦሮሚያ፣ በደቡብ ምዕራብ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ክልሎች፣ በምዕራብ ከሱዳን ሪፓብሉክ መንግሥት ጋር ይዋሰናል፡፡ የክልሉ ቆዳ ስፋት 157,126.83 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ሲሆን የሀገሪቱን 15% ያህል ይሸፍናል፡፡ የክልሉ አስተዳደራዊ መዋቅር ሲታይ በአዲስ መልክ በ14 ዞኖች፣ በ150 የገጠር ወረዳዎች፣ በ52 የከተማ ወረዳ አስተዳደሮች እንዲሁም በ3ሜትሮ ፖሊተን፣ በ4 ሪጆዎ ፖሊተንና በ2 ኢንዱስትሪ ከተሞች የተደራጀ ሲሆን በክልሉ በአጠቃላይ 23,548,998 (በከተማ 5,197,996፤ በገጠር 18,351,002) ሕዝብ እንደሚኖር ይገመታል፡፡

የክልሉ የአየር ንብረት ሁኔታ ቆላ 33.66%፣ ወይና ደጋ 45.14%፣ ደጋ 20.37% እና ውርጭ 0.83% የሚሸፍን ሲሆን መልክዓ ምድራዊ አቀማመጡም ከባህር ጠለል በላይ ከ500 እስከ 4,622 ሜትር የሚደርስ ነው፡፡ አማካይ የሙቀት መጠኑም ከ20° እስከ 25° ሴ.ግ ሲደርስ ዝቅተኛው 10° ሴ.ግ ነው፡፡ ዓመታዊ የዝናብ መጠኑም ከ600-2000 ሚ.ሜ ሲሆን ከዚህም በዓመት ከ50 ቢ.ሜ.ኩ በላይ ውኃ ማግኘት የሚቻል ሲሆን ጥቅም ላይ የዋለው በጣም አነስተኛ ነው፡፡

የክልላችን አብዛኛው ሕዝብ በገጠር የሚኖር ሲሆን ህይወቱ ከመሬት እና ከዝናብ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፡፡ የህዝብ ቁጥር መጨመር፤ የአካባቢ መራቆት እና የከባቢ አየር ንብረት ለውጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ በመምጣቱ ምርትና ምርታማነትን መቀነስ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በሰው ልጅ ህልውና ላይ ፈተና ሆነዋል፡፡

በክልሉ የመስኖ ልማት መጠቀም የጀመርነው ከጥንት ጀምሮ ቢሆንም በዘመናዊ መንገድ መስኖን በስፋት መጠቀም የጀመርነው ከ1980ቹ በኋላ ነው፡፡ ነገር ግን በክልላችን በደረሰው ተደጋጋሚ ድርቅ የተነሳ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በአማራጭነት የሚሰራ ሳይሆን የህልውና መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን በመረዳት ከዝናብ ጥገኝነት ለመላቀቅና ችግሩን ከመሰረቱ ለመቀልበስ የሚያስችል ሥራ ለመሥራት የክልሉና የፌደራል መንግስት ለመስኖ ተቋማት ግንባታ የሚመድቡት በጀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በዚህም መሰረት የዘመናዊ መስኖ አውታር ግንባታ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች በተመሳሳይ ደረጃ የተፈጸመ ባይሆንም፤ ሥራው በተሠራባቸው አካባቢዎች ሲታይ የኅብረተብ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ እና ለብዙ ዓመታት የቆዩ የኅብረተብ ጥያቄዎችን ከመመለስ አኳያ አበረታች ለውጥ ተመዝግቧል፡፡

የመስኖ መሠረተ ልማት የማስፋፋት ሥራን በተሳካ ሁኔታ ጀምረነው እየሰፋ የመጣና የቆዬ የኅብረተብ ጥያቄን የመለሰ ቢሆንም አሁንም በርካታ የሆነ የክልላችን አካባቢዎች የመስኖ አውታር ግንባታ ሥራ አልተሠራባቸውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የኅብረተቡ ጥያቄወች ሙሉ በሙሉ አልተመለሱም፡፡ በክልሉ ሠፋፊ የሆኑ መሬቶችን በመስኖ ማልማት ሲቻል በበጀት እጥረትና በተቋማዊ አቅም ውስንነት የተነሳ የታሰበውን ያህል ማከናወን አልተቻለም፡፡ በሌላ በኩል ተገንብተው ያለቁና ለመስኖ ውኃ ተጠቃሚ ማኅበራት የተላለፉ የመስኖ አውታሮችም ቢሆኑ ብዙ አገልግሎት ሳይሰጡ የሚበላሹ ጥቂቶች ስላልሆኑ ውጤታማ የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት፤ ተቋማዊ ለውጥና ጥንካሬ በመፍጠር ችግሩን መፍታት አስፈላጊ ነው፡፡

በቀጣዩ የእቅድ እና የትግበራ ዓመታት የመስኖ መሠረተ ልማት ግንባታ አሁን ከደረሰበት የአፈጻጸም ደረጃ በመነሳት ዘርፉ ለሚጠይቀው  የመፈጸም ብቃት ዝግጁ መሆን፣ ከተለመደው አካሄድ በመፍጠን በርካታ አማራጮችን መመልከት፣ መቀመርና መተግበር ይጠይቃል፡፡ አመራሩም በአመራር ብቃቱ፣ ባለሙያውም በእውቀቱና ክህሎቱ በኃለ፤ፌነትና በተጠያቂነት የሚሰራበት፣ ከቴክኖሎጅ ስርጸትና አጠቃቀም ከማሳደግ ባሻገር የተለያዩ አጋር አካላት ቅንጅታዊ አሠራር አብዝቶ የሚፈለግበት ከዩኒቨርስቲዎች እና ከምርምር ተቋማት ጋር ተናቦ የሚሰራበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

ክልላሉ በቂ የሚባል የውኃ ሀብትና በመስኖ ሊለማ ሚችል መሬት አለው፡፡  በአራቱ ተፋሰሶች (ዓባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽና ጎሊና ደረቅ ተፋሰስ) በዓመት 44.8 ቢሊዮን ሜትር ኩብ የገጸ ምድር ውኃ እንዲሁም 5.1 ቢ.ሜ.ኩ የከርሰ ምድር ውኃ በድምሩ ከ50 ቢ.ሜ.ኩ በላይ የውኃ ሀብት ይገኛል፡፡  ይህ በእንዲህ እንዳለ ከአፈር ለምነትና የመልክዓ ምድር አቀማመጥ አኳያ ሲታይ 2.2 ሚሊዮን ሄክታር  በመስኖ መልማት የሚችል መሬት እንዳለ በቅርብ የወጡ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

እስካሁን ክልሉ በመስኖ የለማው መሬት 260,269 (11.8%) ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ከመስኖ ልማቱ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ጥቅም ለማረጋገጥ አሁን ከተደረሰበት ሽፋን ወደ 22% በማድረስ የጀመርነውን ጥረት ውጤታማ ለማድረግ ቁልፍ ችግሮች ናቸው ብለን የለየናቸውን ደረጃ በደረጃ በመፍታትና መልካም ልምዶችን በማዳበር ዕቅዱ እንዲሳካ የበለጠ ጥረት ለማድረግ የቀጣዩ አምስት ዓመታት (ከ2018 እስከ 2022) ዕቅድ አዘጋጅቷል፡፡

## 2. የሁኔታ ትንተና

### 2.1 ሀገራዊና ክልላዊ ሁኔታ ትንተና

አገራችን በኢኮኖሚዉ መስክ በ2017 መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ ሀገሮች ተርታ የማሰለፍ ራዕይ ተቀርጾና መግባባት ላይ ተደርሶበት ይህን ራዕይ እዉን ለማድረግ ርብርብ እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል፤ ከዚህ በመነሳት እና ይህን የተጀመረ እንቅስቃሴ በማጠናከር በ2022 በረዥም ጊዜ የእቅድ ዘመን እንደሀገር ለማሳካት የተቀረፀዉን ራዕይና ተልዕኮ በመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ዘርፍ እዉን ለማድረግ የሚኖረዉ ድርሻ ጉልሴህ ቦታ የሚሰጠዉ በመሆኑ በክልሉ ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ ወደ ሀገራዊ ራዕይ ሊያሳካ የሚችል ዕቅድ ለማቀድ ጥረት ተደርጓል፡፡

አገራችን በመስኖ ሊለማ የሚችል ሰፊ መሬት ያላት ቢሆንም በፋይናንስ እጥረት፣ በመፈፀም እና በማስፈፀም ውስንነት፣ በአደረጃጀት ችግር እና መንግስት ለዘርፉ ሲሰጠው የነበረው የትኩረት ማነስ ምክንያቶች በመስኖ የለማው መሬት በጣም ውስን ነው፡፡ ነገር ግን በቅርቡ መንግስት ለዘርፉ በሰጠው ልዩ ትኩረት ተቋሙ እራሱን ችል ከፌደራል እስከ ወረዳ ራሱን ችሎ እንዲቋቋም ከማድረጉም በላይ በዘላቂ ልማት ግቦች በጀት እንዲደገፍ በማድረጉ ጥሩ ጅምሮች አሉ፡፡ የክልሉ መንግስት ለመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንዳለበት በእምነት በመያዝ የሚኒስትር መ/ቤቱ ጋር በቅርበት በመስራት ከፍተኛ በጀት እንዲመደብ ተደርጓል፤

ነገር ግን በአገራችን በተከሰተው ጦርነት ምክንያት እንዲሁም ክልላችን አሁንም ድረስ ጦርነት ውስጥ በመሆኑ በ2015 እና 2016 በጀት አፈፃፀም ላይይ አለታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ በጦርነቱ ምክንያት ያጣነውን ምርት በላላልች አካባቢዎች በመስኖ በማልማት ለማካካስ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፤

በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በታቀደው የ10 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ መሠረት በአገር አቀፍ ደረጃ የመስኖ ጥናትና ዲዛይን ሥራዎች በ2012 ዓ.ም ከተደረሰበት 600,000 ሄክታር በመነሳት በ2022 ዓ.ም 1.6 ሚሊዮን ሄክታር ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በግንባታው ዘርፍም በ2012 ዓ.ም ከተደረሰበት 490,000 ሄክታር በ2022 ዓ.ም 990,000 ሄክታር ለማድረስ ታቅደል፡፡

አጠቃላይ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ የሚሆኑ ምርቶችን በማምረት ለኢንዱስትሪዎች መስፋፋት

ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ዋነኛው ጉዳይ ዘመናዊ መስኖን ማስፋፋት እንደሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ አቅጣጫ ተቋምጧል፡፡

በመሆኑም ከመስኖ ልማቱ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ጥቅም ለማረጋገጥና የጀመርነውን ጥረት ውጤታማ ለማድረግ ቁልፍ ችግሮች ናቸው ብለን የለየናቸውን ማለትም የውስጥ የመፈጸም ብቃት፤በዘርፍ ያለውን የባለሙያ እጥረት፤ቴክኖሎጅን የመጠቀም እጥረት፤የአማካሪዎች የተቋራጮች እና ሌሎች አጋር አካላት አቅም ውስንነት፤በመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ ኅብረተቡን ሙሉ ግንዛቤ እንዲይዝ በማድረግ ተሳትፎውን ያለማሳደግ፤የገበያ ትስስር አለመኖር፤ውኃን በቁጠባ ያለመጠቀም ችግር መኖር፤ የተፍሰስ ልማት ስራዎቻችን ከአነስተኛ፣መካከለኛና ከፍተኛ የውኃ ማጠራቀሚያ ግድቦች ጋር አስተሳስሮ ባለመፈፀሙ ምክንያት በደለል የመሞላት ችግር፤እንዲሁም የኃይል አቅርቦት ችግሮችን እየለዩ ደረጃ በደረጃ በመፍታትና መልካም ልምዶችን በማዳበር የቀጣዩን ስምንት ዓመታት የእቅድ ዘመን እንዲሳካ የበለጠ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 2.2 ተቋማዊ ዳሰሳ /ትንተና

የመስኖ ልማት አፈፃፀም ውጤታማነት የሚለካው በተሰሩ የመስኖ አውታሮች የነዋሪውን ማህበረሰብ ፍላጐትን ለማሟላት ወጪ ለተደረገ ገንዘብ ተገቢውን ጥቅም ማስገኘት መቻሉ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ለመስኖ ልማት ሥራ ከተከፈለ ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም መገኘቱን ለማረጋገጥ የመስኖ ውኃ ጥናትና ዲዛይን፤የግንባታና ክትትል ስርዓቱን የበለጠ ሀብትና ጊዜ ቆጣቢ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተመሳሳይ የጨረታ ሂደታችን የተገነቡ የመስኖ ተቋማትን የማስተዳደሩና የውኃ ተጠቃሚ ማህበራትን ማድረጉ ተጠያቂነትን የተላበሰ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ቀልጣፋና ግልፅ አሰራርን መሠረት አድርጐ በውድድር ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የሚያስችሉ አደረጀጀቶች እንዲኖሩት በክልሉ መንግስት ታምኖበት የአብክመ መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 መሰረት እንዲቋቋም ተደርጓል ፡፡

የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ በአንድ ቢሮ ኃላፊ፤ ሁለት ምክትል ቢሮ ኃላፊዎች እና ሁለት አማካሪዎች፤ስምንት ዳይሬክቶሬቶች (የመስኖና ድሬኔጅ ጥናትና ዲዛይን፤የመስኖ ድሬኔጅ ግንባታ ክትትል፤የመስኖ ተቋማት ግብአት አቅርቦት፤የመስኖ ተቋማት አጠቃቀም አስተዳደርና ጥገና፤የዕቅድና በጀት ዝግጅት ክትትልና ግምገማ፣ የህዝብ ግንኙነት፣ የግዥና ፋይናንስ ንብረት አስተዳደር እና የሰው ሀብት ሥራ አመራር ክፍሎች) ተዋቅሯል፡፡

### 2.2.1 ውስጣዊ ሁኔታዎች (ጥንካሬና ድክመት)

ለቀጣዩ ዓመት ዕቅድ አስተዋጽኦ የሚኖራቸዉ ምን ምን ጥንካሬዎች እንደነበሩና መታረም ያለባቸዉና በተግባር ሂደት ተከስተዉ የነበሩ ዋና ዋና ድክመቶችን ተንትኖ ማየቱ ከፍ ብሎ እንደተጠቆመዉ በቀጣይ ችግሮችን መፍታት የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ለማድረግና ጥንካሬወችን አጎልበቶ ለመጓዝ ስለሚአግዝ ዉስጣዊ ሁኔታዎችን በሚከተለዉ መልክ ጠቅለል አድረጎ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

### ሀ. ጠንካራ ጎኖች

ቢሮዉ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ዕቅዶችን ነድፎ በመፈጸም ረገድ ያካበተዉ ልምድና በተለይ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ የተገኘዉ ተሞክሮ የሚያበረታታ ስለሆነ ልምዱ ለቀጣዩ ዓመታት መርሀ ግብር ጉልህ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ በየደረጃዉ የተሰማራዉ ፈጻሚ ሀይል የሙያ ብቃቱን እንዲያጎለብትና የመፈጸም አቅሙን እንዲያሳደግ በየጊዜዉ የአጭር ጊዜ ስልጠና መሰጠቱ በዘርፉ የሚታየዉን የባለሙያ ችግር ለመቅረፍ ጉልህ ሚና ያለዉ ነበር፣ቢሮው አቅም በፈቀደ መጠን በቀሳቅስና በመሳሪያዎች ለመደራጀት የተሞከረ መሆኑ ስለሆነም ይህ ተግባር የበለጠ ጎልብቶ ሊቀጥል ይገባል፡፡

የቢሮው የማስፈጸም አቅም እየተሻሻለ መምጣቱ፣ከወረዳ እስከ ክልል በየደረጃዉ የተሰማራዉ ፈጻሚ ሀይል የሙያ ብቃቱን እንዲያጎለብትና የመፈጸም አቅሙን እንዲያሳደግ በየጊዜዉ የአጭር ጊዜ ስልጠና መሰጠቱ በዘርፉ የሚታየዉን የባለሙያ የሙያ ችግር በመጠኑ ለመቅረፍ ተሞክሯል፣ ስለሆነም ይህ ተግባር የበለጠ ጎልብቶ ሊቀጥል ይገባል፣

የተቋማችን አደረጃጀት ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ መኖሩ ፕጀክቶች ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ፣ በወቅቱ እንዲጠናቀቁ የፕሮጀክቶች ክፍያ ያለብክነት ለመፈፀም የሚያስችል በመሆኑ ጠቀሜታው እጅግ ያላቀ ነው፣ ደንቦችና የአፈፃፀም መመሪያዎች እንዲሁም ማንዋሎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እየዋሉ መሆኑ፣በቡድን የመሥራትና ልምድን የማካፈል፣ በማኔጅመንት አሳታፊ በሆነ መንገድ በጋራ የመወሰን ባህል መኖር፣በቢሮው ክህሎትና ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎች መኖር፤ በሰው ሀይል ልማት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠና መሰጠቱና ከአቻ ተቋማት ልምድ መወሰዱ፤የቢሮው የማስፈጸም አቅም እየተሻሻለ መምጣቱ፣የመስኖ ልማት ሽፋን እየጨመረ መምጣቱ፣የቢሮዉ ቁልፍ አጋርና የትልልቅ ፕሮጀክቶቻችን ፈጻሚ የሆኑት የመንግስት የልማት ድርጅቶች እንዲሁም ከሌሎች ከኮንትራክተሮችና አማካሪ ድርጅቶች ጋር ወርሀዊ የሶስተዮሽ የምክክር መድረክ በቋሚነት

በመፍጠርና ስራዎችን በመገምገም ለፕሮጀክቶች መጓተት ምክንያት የሆኑ ችግሮች ለመፍታት የተደረገዉ ጥረት በጥንካሬ ሊጠቀስ የሚገባዉ ተግባር ስለሆነ ወደ ፊትም በዚህ ዙሪያ ሰፊ ስራ መስራት አስፈላጊ ነዉ፤

የመልካም አስተዳደር ችግር ያለባቸዉን ፕሮጀክቶች በየጊዜዉ እየለዩ ከመደበኛ ስራዎች ጎን ለጎን በልዩ ትኩረት የጊዜ ሰሌዳ ወጥቶላቸዉ ለመፍታት የተደረገዉ ጥረት በበጎ ጎኑ የሚታይ ሲሆን ይህን እቅስቃሴ በማጠናከር የበለጠ አጠናክሮ መቀጠል ይጠበቃል፡፡

**ለ. በእጥረት የታዩ ጉዳዮች**

ይሁን እንጅ መረጃዎችን የማደራጀት ፣የመቀመርና በጥራት የመያዝ ልምድ ችግር በዚህም ምክንያት በክልላችን በትክክል የለማዉን መሬት መጠን ለማዎቅ አስቸጋሪ መሆኑ፤ የዲዛይን ጥራት ችግር መኖር፤የኮንትራት አስተዳደር አቅም ዉስንነት መኖር፤ወደ ግንባታ የሚገቡ ፕሮጀክቶችን የተሟላ ክትትል ለማድረግ የአቅም ዉስንነት ከመኖሩ ባሻገር ተገቢዉን የዲዛይን ማሻሻያ በወቅቱ ባለመስጠት ለተጨማሪ ወጪ መዳረግ ለቀጣዩ ይህንን ክፍተት ለመሙላት የፈጻሚወችን አቅም በቁጥርና በጥራት አሳድጎ ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ለማድረስ መንቀሳቀስ ለነገ የማይባል ነዉ፤

የህብረተሰቡን የተቋማት ባለቤትነት ግንዛቤ አሁንም ጅምር እንቅስቃሴ ቢኖርም በተሟላ መልኩ አስርጸናል ማለት አይቻልም ስለሆነም በቀጣዩ ዕቅዳችን ትኩረት ሰጥተን ልንፈጽመዉ የሚገባ ተግባር ነዉ፤

የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመፍታት የሚጠበቀውን ያህል አለመተግበሩ፤ የክትትልና ግምገማ አሠራር በጥራትና በውጤት ላይ ያተኮረ አለመሆን፣ አገልግሎት አሰጣጡ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አለመሆን፣የባለሙያዎች፤የተቋራጮችና የወረዳ አስተዳደሮች የመፈጸም አቅም ዉስንነት፤የጠራ መረጃ የመያዝ ውስንነት መኖርና መረጃ አያያዙም በቴክኖሎጂ አለመደገፉ፣ለስራ ምቹ የሆነ በቂ የቢሮ መገልገያ አለመኖር እና ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ተሽከርካሪዎችና የቢሮ ቁሳቁሶች አለመሟላታቸው (በተለይ ዞንና ወረዳ)፣ እንዲሁም የመሰረተ ልማት አለመስፋፋት የግንባታ እቅዎችን ለማጓጓዝ ባለመሬቶች መሰናክል መሆን የመስኖ አውታሮችን በተፋጠነ ሁኔታ ለማጠናቀቅ ከፍተኛ ተግዳሮቶች ስለሆኑ ሁሉም አካል በመረባረብ ሊፈቱ ይገባል፡፡

ተቋማችን የነበረበትን ያለፉትን ሶስት አመታት ወደኋላ በመመልከትና በአንክሮ በመረደት ጥንካሬዎች በነበሩበት እንዲቀጥሉና በተግባር ሂደት ተከስተዉ የነበሩ መታረም ያለባቸዉ

ድክመቶችን በመለየት ለመቀነስና ጨርሶ ለማስወገድ እንዲያስችል እንደሚከተለው ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

## 2.3. ስትራቴጅክ ጉዳዮች ትንተና

### 2.3.1 የሰው ኃይል ልማት

በ2022 መገባደጃ ለመስኖ ስርዓቱ የሚፈለገው የሰው ኃይል ብቃት ይገነባል፤የመስኖ ልማታችን የሚጠበቅበትን አስተዋፅዖ እንዳያደርግ ከገደቡት ተግዳሮቶች ዋነኛው የሰው ኃይል ዕውቀት፤ ክህሎትና አመለካከት ውስንነት ነው፡፡ የባለሙያ ብዛት፣ የሙያ ደረጃ፣ የሙያ ዘርፍ፣ የሙያ ስብጥር፣ የልዩ ክህሎት (specialization) ውስን መሆን ዘርፉን አንቀው ይዘውታል፡፡ በተለያዩ ሙያ ዘርፎች ተፈላጊ የትምህርት ደረጃና ዝግጅት ያለው በቂ የሰው ኃይል ከመነሻው ማግኘትና ማዳረስ፣ በአጭር ጊዜ ብቁ የሰው ኃይል ለማሰልጠን የሚችል ባለሙያ በተወሰኑ ሙያ ዘርፎች ላይ ማግኘት፣እንዲሁም የሰው ኃይል ፍላጎትን በሙያ ደረጃ፣ በሙያ ዘርፍ፣ እና በቁጥር ዘርዝሮ ማወቅና በግልፅ መለየት ጭምር ተግዳሮት እንደሆኑ ተለይተዋል፡፡ በዝናብ መጠን ላይ የተመሰረተ የመስኖ ስርዓት፤ ስለዝናብ ሁኔታ በቂ እውቀት ያለው የሰው ኃይል መኖርን ይጠይቃል፡፡ የክልላችንን ለመስኖ ተስማሚ የሆኑ አካባቢዎችን፣ የውሀ መጠንና ስርጭት፣ ለየአካባቢው ተስማሚና ላቅ ያለ ዋጋ ያላቸውን ሰብሎች የመምረጥና የአመራረት ስርዓት፣ ለተለያዩ የመስኖ ዓይነቶች ተስማሚ የሆኑ ቴክኖልጂዎችን አመራረጥና አጠቃቀም በሚገባ ሊረዳ የሚችል ሀገራዊ እውቀትን የተላበሰ የሰው ኃይል ማፍራት በፍጥነት መጀመር ይኖርብናል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ከጥብቅ እርሻ መስኖ ልማት ጋር በተያያዘ ዘመኑ የደረሰበትን የውሀ አጠቃቀም፣ የግሪን ሀውስ ጣራ ሥራዎች ግንባታና እና ንድፈ ስራን የተላበሰ እውቀት ያለው ባለሙያን ማፍራት ይጠበቃል፡፡

በመስኩ በዓለም ደረጃ እየተተገበሩ ያሉ ዘመናዊ ቴክኖልጂዎችን እንደየአካባቢው ሁኔታ በማገናዘብ መምረጥና መጠቀም የሚችል ባለሙያ ልናፈራ ይገባል፡፡ የተራራ ላይ መስኖ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ የሰው ሀይል እንዲኖር ይፈለጋል፤ ይህን የመስኖ ሥርዓት በተመለከተ የመሬትን አቀማመጥ የተጠቃሚውን አሰፋፈርና የኑሮ ሁኔታ በማየት ለመስኖ ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጅዎችን አመራረጥና አጠቃቀም በሚገባ ሊረዳ የሚችል አገራዊ ዕውቀትን የተላበሰ የሰው ኃይል ማፍራት ይጠበቅብናል፡፡

### 2.3.2 የመስኖ ቴክኖልጂ

በእጃችን ባሉትና በቅርብ በምናገኛቸው የአየር ንብረት፣ የጎርፍ ሁኔታ፣ የአፈር፣ የሰብል፣ እና የቴክኖሎጂ መረጃዎችና ያለንን ባለሙያዎች እና ልምዶችን አሰባስቦ፣ ተስማሚ ሆነው በሚመረጡ አካባቢዎች የመስኖ እና የውሀ ማሰባሰብያ መንገድችን በማስጀመር፣ በሂደት አቅምን እያጎለበቱ በስፋት አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድረግና ልማቱን የማስቀጠል ስራ ይሰራል። ውሀን በኩሬ ማሰባሰብን፣ በማሳ ውስጥ አሰባስቦ መጠቀም እና በአጭር ጥልቀት የሚገኝ የከርሰ-ምድር ውሀን ለመስኖ የመጠቀም አማራጭን አርሶ አደሮች እንዲጠቀሙ ከማበረታታት በተጨማሪ ትልቅ ኢንቨስትመንት የሚጠይቁ ከፍተኛ የውሀ መጠን የሚይዙ ግድቦችን፣ ጥልቅ ጉድጓዶች እና በወንዝ ጠለፋ የሚሰሩ መሰረተ ልማቶችን በመንግስት ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ይጠበቃል።

የደጋፊ (Supplemental) እና የጎርፍ (Spate) መስኖ ልማት (ጥናት፣ ግንባታ፣ የእርሻ ስራ ወዘተ)፣ እሉታዊና ወቅታዊውን የዝናብ ሁኔታና የሰብሎችን የውሀ ፍላጎት መሠረት ያደረገ እንዲሆን ይደረጋል። ይህን የመስኖ ልማት ስርዓት ለመተግበር እንዲያመች ተደርገው ሰብል ከመዘራቱ በፊት የእርሻ መሬቶች ይዘጋጃሉ። በሚቀጥሉት ዓመታት የዚህ መስኖ ቴክኖሎጂ ሀገራዊ የሽፋን ሁኔታ እየቀነሰ የሚሄድና በዘመናዊ ቴክኖልጂዎች እየተተካ የሚሄድ ይሆናል። የማርከፍከፍ (sprinkler) መስኖ በቀጣዩ የ5 ዓመት የዕቅድ ወቅት በሀገራችን ተስማሚ የሆኑ አካባቢዎች ላይ በስፋት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል። በተመሳሳይ መልኩ ጠብታ (drip) መስኖ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ሰብሎች፣ ፍራፍሬዎች፣አበባዎችን፣ ለማልማት የምንጠቀምበት ቴክኖሎጂ እንዲሆን ይደረጋል።

የክልላችን የመስኖ ልማት በቀጣዩ 5 ዓመት መገባደጃ ላይ ከመስኖ የሚገኘውን የምርት መጠን ለመጨመር የሚያስችሉ አንድ ማሳ ላይ የሚኖረውን የምርት ድግግሞሽ (irrigation intensity) የማሳደጊያ በአንድ ጊዜ ተደጋጋፊ የሆኑ ሁለት ዓይነት ሰብሎችን የማልሚያ ስርዓትን (double cropping system) እና የደጋፊ መስኖ መንገዶችን እንጠቀማለን።

ከዚህ ዕቅድ በመነሳት በ2042 የክልላችን መስኖ ልማት በረቀቁ ቴክኖሎጂዎች አማካኝነት ውሀን ለተክሎች ተቆጣጥሮና መጥኖ መስጠት (Precision irrigation) የሚችል፣ ራስ አገዝ የመስኖ ቴክኖልጂዎችን (automated technologies) የሚጠቀም፣ ሰው አልባ በራሪ አካላት (Self-

guided drones) ፣ ተንቀሳቃሽ ስልኮችና ድረ-ገፆችን በተወሰነ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ በሚችልበት ቁመና ላይ የሚገኝ ይሆናል፡፡

የመስኖ ውሀ ክፍያ ስርዓትን በመዘርጋትና በመከታተል ለመስኖ እድሳትና አገልግሎት የሚውሉ ወጪዎችን ተጠቃሚዎች እንዲችሉ ይደረጋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በጨው የተበሉ መሬቶችን በማከምና እንዲሁም የመስኖ ውሀ አጠቃቀምና ትርፍ ውሀ የማስወገድ ስራዎችን ተግባራዊ በማድረግ ሁሉም የመስኖ ማሳዎቻችን ከጨዋማነትና (salinity) ከከርሰ-ምድር ውሀ ከፍታ መጨመር (water logging) የፀዱ የማድረግ ስራ የሚሰራ ይሆናል፡፡

### 2.3.3 የመስኖ ምርምር

አሁን ካለንበት ጎታች የምርምር ስርዓት በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰብሮ በመውጣት በመስኖ ምርምር ልቀው ከሄደት ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ፣ በመነሻ ጊዜያት ላይ ያሉትን የምርምርና ስልጠና ተቋማትን አሰባስቦ መጠቀም፣ ወሳኝ ቴክኖሎጂዎችን አስገብቶ የማላመድ፣ ቁልፍ ክልላዊ ችግሮች ላይ የማተኮር፣ የምርምር ማዕከላትን የመዘርጋትና አቅምን ማጎልበት፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የማፍለቅና በቀጣይነት እያጎለበቱ መሄድ፣ ጠንካራ ሀገራዊና አለማቀፋዊ ግንኙነትና ትስስርን የመዘርጋት፣ ሀገራዊና ክልላዊ የስርጸትና የስልጠና ስራዎችን የማስፋፋት እንዲሁም የምርምር ውጤቶች ህትመትንና ተደራሽነትን የመዘርጋት የመሳሰለ አቅጣጫዎችን መከተል ያስፈልገናል፡፡

በክልላችን የዝናብ ሁኔታ ላይ በመመስረት ሁለት የምርምር ስርዓቶች የሚገነቡ ይሆናል፡፡ እነዚህም በቂ ዝናብ የሚያገኙ እና የዝናብ እጥረት ያለባቸው ናቸው፡፡ በቂ ዝናብ የሚያገኙ ቦታዎች የምንከተለው የአጭር ጊዜ መስኖ ምርምር ስርዓት ሲሆን የዝናብ እጥረት ለሌለባቸውና የስርጭት መዛባት ላለባቸው አካባቢዎች የረጅም ጊዜ እና ተደጋጋሚ የድርቅ ወቅት መስኖ ስርዓት ነው፡፡ ይህ በተለይ ከከባቢ አየር ለውጥ ሁኔታ ጋር በቀጥታ የሚያያዝ እና የረጅም ጊዜ ጥናት እና ምርምር ስራ እነደመሆኑ መጠን ቀጣይነት ያለው የረጅም ጊዜ መረጃ አሰባሰብ ስርዓት በውስጡ የያዘ ይሆናል፡፡ እንደ ማንኛውም ምርምር ሁሉ የታሰቡ ወይም እየተተገበሩ ያሉ የመስኖ ልማት ስርዓቶችን ዲዛይን፣ እቅድ እና አፈፃፀማቸውን በማገናዘብ ስርዓቱን ማሻሻል የሚቻልበትን መንገድ እንዲያሳይ ይደረጋል፡፡

በቆላማ አካባቢዎች ውሀ እጅግ ውድ ሀብት በመሆኑ ቀደም ሲል እንደተገለፀው በምርምር መረጃ የተደገፈ ውሀ ቆጣቢ የሆኑ ዘመናዊ የመስኖ ቴክኖልጂዎች እና የሰብል አመራረት

ስልቶችን ስራ ላይ በማዋል በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ ማምረት የሚቻልባቸው ምርምሮች ይከናወናሉ። በአንፃራዊ ሜዳማ ስፍራዎች ላለው ትኩረት የሚሻው ጉዳይ ትርፍ ውሀን ማስወገጂያ ወይም መልሶ መጠቀም የሚያስችሉ መንገዶችን በመተግበር የመስኖ እርሻዎችን ከጨዋማነት መከላከል እና ውሀን በአግባቡ መጠቀም የሚቻልበትን መንገድ በጥናት እና ምርምር የተለዩ ዘዴዎችንና ስልቶችን ማላመድ፤መጠቀምና ማፍለቅ ይሆናል ። አንፃራዊ ሜዳማ መሬቶቻችን በአብዛኛው የአርብቶ አደር አካባቢዎች እንደመሆናቸው ለእንስሳት መኖ ማምረትና አስተማማኝ መኖ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ የሚያገለግል የምርምር እና ጥናት ስራዎችም ይከናወናሉ።

### 2.3.4 የመስኖ መሰረተ ልማት

በመስኖ ስርዓቱ መሰረተ ልማት ስትራቴጂያዊ ቁመናችንን ክልል አቀፋዊ ብቃት ያለው ለማድረግ በክልላችን የሚገኘውን የገፀ-ምድር ውሀ ሀብት በሁሉም ጅረቶች ላይ እንደ ውሀ ፍሰት አቅማቸው ግድብ በመስራት የከርሰ-ምድር ውሀ ሀብታችንን ደግሞ የውሀ ኡደት ሚዛንን (hydrologic balance) እንዳያዛባ በመጠበቅ ተገቢውን መሰረተ ልማት በመገንባት ማሰባሰብ፤በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚፈጠሩ መልካም አጋጣሚዎችንም ሆነ ስጋቶችን ያማከለ ግብርና ለመገንባት አሁን ያሉት የመስኖ ፕሮጀክቶች በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩ ማድረግ፤ በክልል መንግስት እንዲሁም የግል የሆኑ ለመስኖ ስርዓቱ መዳበር በጥናት፣ በንድፍ፣ በግንባታ፣ በምክር፣ በጥገና፣ በቁጥጥር እና በስልጠና ስራ ላይ የሚሰማሩ ተቋማትን በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ አቅማቸውን በመገንባት፣ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ መደገፍ፣ በተጨማሪም ክልላዊ ሽፋን ያለው የመረጃ ልውውጥ ስርዓት በመዘርጋት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግን እንደአፈፃፀም አቅጣጫ የምንወስዳቸው ይሆናሉ።

የመስኖ መሰረተ ልማት ግንባታና የመስኖ ውኃ  አቅርቦት ከኃይል ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ስላለው የጸሐይ ኃይልንና ከውኃ ታዳሽ ኃይል ጋር አስተሳስሮ ለመስራ ጥረት ይደረጋል።

### 2.3.5 የመስኖ ስራ አደረጃጀት

ክልላችን ብሎም አገራችን ከድርቅ እና ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ የምግብ ሉዓሊዊነታችንን ለማረጋገጥ ፍትኃዊ የመስኖ ልማት አጠቃቀም ስርዓት መገንባት ይኖርብናል። የመስኖ ውሀ አጠቃቀምን ማዘመን በውሀ አጠቃቀም ዙሪያ ሊከሰቱ የሚችሉ ያለመግባባቶችን ለማስዘብ እና ፍትኃዊ የመስኖ አጠቃቀምን ለማዳበር እና አመለካከቶችን ለማስረፅ ይረዳል።

የመስኖ ስራ አደረጃጀት እና የባለድርሻ አካላት ትስስር አንፃር በማመሳከር የተቀናጀ የመስኖ ባለድርሻ አካላት ትስስር (Interconnectivity) መፍጠርን፤የተቀናጀ የውሀ ሀብት ልማት አስተዳደር ተግባራዊ ማድረግን፤ በሀገራችን ያለ አነስተኛ መስኖዎችን ለተደራጁ የአካባቢው ወጣቶች የስራ እድል መፍጠርያ ማድረግን፤ ሀገራዊና ክልላዊ ወቅታዊ ችግሮች ላይ ትልቅ ትኩረት አድርጎ የውሀና መስኖ ጥናት፣ ምርምርና ስልጠናን የሚያስተባብርና የሚመራ ጠንካራ ክልላዊ ተቋም ማቋቋምን እና በቅርብ የሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞችን፣ የጥናት እና ምርምር ማዕከላትን፣የግንባታ ስራ ተቋራጮችን በስብስብ (Clustering) ስርዓት መዘርጋትና ጠንካራ ክልላዊና ሀገራዊ ብሎም ዓለማቀፋዊ ግንኙነት መፍጠርን የመስኖ ስራ አደረጃጀትና ትስስር ስርዓት ሀገራዊውን የመስኖ ልማት ስርዓት በማዘመን ዓለም አቀፋዊ ቁመና ላይ ለማድረስ የሚያስችለን የአሰራር አቅጣጫዎች ተደርገው ተወስደዋል፡፡ እነዚህ አሰራር አቅጣጫዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሌሎቹ አስቻይ ብቃቶች ስር የተዳሰሱ ሲሆኑ የመስኖ የውሀ ምደባ እና የክፍያ ስርዓት መዘርጋት እና በዕቅድ ላይ የተመሰረተ ፍትኃዊ የመስኖ አጠቃቀምና ህጋዊ የአሰራር ስርዓት እንዲኖረው ማድረግ የምንከተላቸው የአፈፃፀም አቅጣጫዎች ይሆናሉ፡፡

## 3. ርዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች

### ራዕይ

በ2023 ዓ/ም ክልሉ ያለዉን እምቅ የመሬት ሃብት በመስኖ በማልማት የክልላችንን የምግብ ሉአላዊነት ተረጋግጦ ማየት፤

### ተልዕኮ

በክልሉ ያለውን ሰፊ የመስኖ ልማት አቅም በመለየት አሳታፊና ጥራት ያለው የጥናት፣ ዲዛይን እና ግንባታ ስራ በማከናወን፤ ተስማሚ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የመስኖ ተቋማትን በማስተዳደርና ለቆላማ አካባቢዎች ልማት ልዩ ትኩረት በመስጠት ህብረተሰቡን በዘላቂነት እና በፍትሃዊነት ተጠቃሚ ማድረግ፤

### እሴቶች

- ፍትሃዊነት
- አሳታፊነት
- ታማኝነት
- ቅንነት

- አገልጋይነት
- በቡድን መስራት
- ሆኖ መገኘት

## 4. የዕቅዱ መነሻዎች

## 4.1 ያለፉት በጀት ዓመታት አፈፃፀም እንደ መነሻ

### 4.1.1 ከቁልፍ ተግባር አኳያ ሴክተሩ ያለበት ሁኔታ

*ሀ. አመለካከት*

እንደሚታወቀው የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ሲደራጅ ተግባራትንና የሰው ኃይልን ከውኃና ኢነርጂ ቢሮ እንዲሁም ከግብርና ቢሮ የተረከበ ቢሆንም የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ግምት ውስጥ ያስገባ በላቀ ደረጃ የሕዝብን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ሊያረጋግጥ የሚያስችል ከእትዕ-2 የተቀዳ ከሁለቱም ቢሮዎች የነበሩ ሠራተኞች ባለፉት ዓመታት በሙሉ ርብርብ ሲደረግ መቆየታቸው ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በሙኑም መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ከተቋቋመ ጀምሮ ከሁለቱም ቢሮዎች የመጡትን ሠራተኞች ከከፍተኛ አመራሩ ጋር እንዲሁም እርስ በርሳቸውም እንዲተዋወቁ በማድረግ ዕቅዱን በማስተዋወቅ አፈፃፀሞችን በየሩብ ዓመቱ በመገምገም ሠራተኛው በአመለካከት አንድ እንዲሆን ለማድረግ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

የልማት ሠራዊት መሪ የሆነው አመራር በየደረጃው የሠራዊት መሪነት ሚና እንዲጎናጸፍ ስልጠና እና በዕቅዶች ላይ ኦረንቴሽን በመስጠት እና ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ተግባራትን በመምራት በኩል አበረታች ውጤቶችን በሁሉም ደረጃ ማስመዝገብ ተችሏል፡፡ በተለይም ከፍተኛ አመራሩ ሴክተሩ የተሟላ ቁመና እንዲኖረው አደረጃጀቶችንና አሰራሮችን በመፈተሽ፤ የማሳተካከያ እርምጃ በመውሰድና የተሻለ ግብዓት እንዲቀርብ በማድረግ ፤ በተጠቃሚው ኅብረተሰብ በኩል ሠፊ የሆነ ግንዛቤ ፈጠራ ሥራ በመሥራት ተጠቃሚው ኅብረተሰብም የባለቤትነት ስሜት ፈጥሮ ተሳትፎውን በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር በማድረግ የተሰራው ሥራ አበረታች ነበር ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ለጋሽ ድርጅቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንደ ልማት አቅም በመውሰድ ሀብታቸውን በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ለማስቻል ፕሮጀክቶችን በመምራትና በማስተዳደር፤ለሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ በማስጨበጥ በኩል የተሰሩት ሥራዎች አበረታች ነበር፡፡

ተቋሙ በቅርብ የተቋቋመ ቢሆንም የዞንና የወረዳ መዋቅር እንዲፈቀድ በማድረግ የዞንና ወረዳ ላሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ስለተቋሙ ርዕይ፣ ተልዕኮና ዋና ዋና ተግባራቶች መሰረታዊ መረጃ እንዲይዙና ተግባሮቻቸውን አውቀው እንዲመሩ ግንዛቤ ለማስጨበት ተሞክሯል፡፡ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚ ማኅበራት ኮሚቴዎች በየጊዜው ሥራቸውን እንዲከታተሉ ለማድረግ በተፈጠረው የንቅናቄ መድረክ ተጠቃሚው ኅብረተብ በነባርም ሆነ አዲስ በሚገነቡ የመስኖ ተቋማት ዙሪያ ሠፊ ግንዛቤ በመፍጠር በእቅዶችም ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖር ሲደረግ የቆየ ቢሆንም የመስኖ ውኃ ተጠቃሚ ማኅበር የኮሚቴ አባላት ተቋሙን እንዲመሩትና እንዲያስተዳድሩት የመሪነት ሚናቸውን በመወጣት የተቋሙ ባለቤት ተጠቃሚው ኅብረተብ እንደሆነ የተያዘው ግንዛቤ ከመነሻው አናሳ የነበረ እና በሂደት እያደገ የመጣ ቢሆንም የአመለካከት ለውጡ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

ይሁንና በተጠቃሚው ኅብረተብ ዘንድ በአመለካከት በኩል የመጡ ለውጦች ቢኖሩም በአመራሩ በኩል ተግባራትን የሕዝብን ሙሉ አቅም ተጠቅሞ ለመሥራት የሚደረግ ጥረት፤ ባለሙያውን እና ኅብረተቡን በአመለካከት ቀይሮ የልማት አጋዥ ለማድረግ የተደረገው ጥረት፤ የለውጥ መሳሪያዎችን በእምነት ተቀብሎ ባለሙያውን አሳምኖ እንዲተገብራቸው በማደረግ፤ የመንግስትን ወይም የአጋር አካላትን በራስ ተነሳሽነት ተሳትፎን ከማሳደግ አኳያ፤ የመስኖው ዘርፍ ለግብርና ልማታችን ብሎም ለኢንዱስትሪ ትራንስፎርሜሽን የአለውን ጠቀሜታ በውል በመገንዘብ ተግባራዊ በማድረግ በኩል የሚቀርና ውስንነት የነበረበት ነው፡፡

በባለሙያው በኩል በዋናነት የሲቪል ሰርቪሱን አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ፤ ዘመናዊ፤ ተደራሽ ለማድረግ ተብለው የተቀረፁትን የለውጥ መሳሪያዎችን የፖለቲካ መዋቅር ወይም ግብ ማስፈፀሚያ አድርጎ የመቁጠርና ለተግባራዊነቱም ለይስሙላ እንጂ በእምነት ይዞ ከመሥራት አንፃር ሠፊ ውስንነት እንደነበረበት ይታወቃል፡፡ በተጨማሪም ሥራን አክብሮ በመሥራት ለውጥ ለማምጣት እና በመጣው ለውጥም ሕዝቡ ሲጠቀም በየደረጃው ተጠቃሚ እሆናለሁ ብሎ ከመሥራት ይልቅ በጊዜያዊ ጥቅም ላይ ትኩረት ማድረግ፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ባለሙያው አላስፈላጊ ምክንያቶችን በማንሳት የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን መጠየቅ፤ ውጤትን ሳይሆን መውጣት መውረድን እንደ ስኬት መቁጠር፤ ከአመራሩ ጋር እጅና ጓንት ሁኖ አለመሥራት በባለሙያው የሚስተዋሉ የአመለካከት ችግሮች እንደነበሩ ይታወቃል፡፡

በተመሳሳይ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚ ማኅበራት የተገነቡ የመስኖ ተቋማትን ተረክቦ በአግባቡ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ከመስጠትና ራስን ችሎ ከማስተዳደር ይልቅ የጠባቂነት ስሜት በከፍተኛ ደረጃ የሚስተዋልበት ነበር፡፡

በአጠቃላይ በአመራሩ፤ በባለሙያው በአጋር አካላትና በተጠቃሚው ኅብረተብ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት ሠፊ ሥራ የተሰራ ቢሆንም በተሰራው ልክ ሙሉዕ የሆነ የአመለካከት ለውጥ መጥቷል ብሎ መውሰድ አይቻልም፤ በቀጣይ መሠራት ያለበት ሰፊ ስራ እንዳለ ያሳያል፡፡ ስለዚህ የተጀመረውን የአመለካከት ለውጥ ከሚፈለገው ግብ ለማድረስ በሚያስችል መንገድ በየደረጃው አጠናክሮ መሥራትን ይጠይቃል፡፡

**ለ. ከክህሎት አኳያ**

የሠራተኞችን ክህሎት ለማሳደግ የአጭር፤ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ስልጠናዎች በስፋት ሲሰጥ የቆየ ሲሆን በተለይም በጥናትና ዲዛይን እንዲሁም በግንባታ ክትትል ሲሰሩ ለነበሩ ፈጻሚ ባለሙያዎች የተሰጡ ስልጠናዎች አበረታች እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏላል፡፡ የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮም እንደተቋቋመ ለመሀንዲሶች ፤ ለጂኦሎጂስቶችና ለቀያሾች የተደራጀ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች ተሰጥቷል፡፡ ከክህሎት ማሳደጊያ ስልጠናዎች በተጨማሪ የዲዛይን ክለሳ / Design Review / መድረኮችንና የሦስትዮሽ ውይይቶችን በማድረግ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች ክህሎት እንዲያድግ ለማድረግ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

የሴክተሩ አመራር እያደገ የመጣ ሀብትን መሠረት ያደረገ፤ የመንግስትን አቅጣጫን የተከተለ፤ የሕዝብን ፍላጎት፤ የተፈጥሮ ጸጋን፤ ዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀሞቻችንን መሠረት ያደረገ ዕቅድ የማቀድና የመተንተን ችሎታው በሂደት እያደገ መጥቷል፡፡ ዕቅድን በተሟላ መንገድ ለማስፈጸምም የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ፤ግብረ መልስ በመስጠት የባለሙያውንና የኅብረተቡን አመለካከት ለመለወጥ የተደረገው ጥረትም በቀለላሉ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ አመራሩ ዕቅዱን በተደራጀ መንገድ በማቀድና በመተንተን እንዲሁም ባለሙያውና ኅብረተቡን ባለቤት በማድረግ ሂደት የአሰተሳሰብ ለውጥ የማምጣት ሥራ የሚቀር ተግባር እንደሆነ ግንዛቤ መያዝ ይኖርበታል፡፡

የመፈፀም አቅም በሁሉም ደረጃ አኩል ማምጣት ባይቻልም ቢያንስ ዞኖችን ከዞኖች ወረዳዎችን ከወረዳዎች ለማቀራረብ የክትትልና የድጋፍ ሥርዓትን በተቆራረጠ አግባብ ቢሆንም የተለያዩ

አማራጮችን በመጠቀም ለመደገፍ የተሄደበት ርቀት፤ የመፈፀም አቅማችን እንዲያድግ እና ሀብትን በአግባቡና በቁጠባ ለመጠቀም የተደረገው ጥረት ሠፊ መሻሻል የተገኘበት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

ዕቅድን በዕውቀት ላይ ተመስርቶ ለመፈጸም የፈጻሚዎችን ሙያዊ ክህሎት ማሳደግ ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም በተለያዩ የሙያ መስኮችና የስልጠና ጊዜያት በአጭር ጊዜና በረዥም ጊዜ ስልጠና ከመጀመሪያ ዲግሪ እስከ ሶስተኛ ዲግሪ ሠራተኞችን አቅዶ በማሰልጠን ሠራተኞችን በተለየ የሙያ ክህሎት እና ዕውቀት ለመገንባት በተለያዩ የስልጠና ፕሮገራሞች ከማስተማር ባሻገር በወቅታዊ አሰራሮች ላይ ተመርኩዞ አጫጭር ስልጠናዎችን እንዲሰጡ ማድረግ በትኩረት የሚሰራበት ይሆናል፡፡

### ሐ. ከአደረጃጀት አኳያ

የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት መሠረት በማድረግ የኅብረተቡን በመስኖ ልማት ተጠቃሚ ለመሆንና በዘርፉ የሚነሳውን ሠፊ ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል የሰው ኃይል አደረጃጀት አጥንቶ ወደ ስራ የገባ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የሰው ኃይሉን በማደራጀት ለተግባራዊነቱ ፈጥኖ ወደ ሥራ በመግባት ያደረገው እንቅስቃሴ በበጎ ጎኑ የሚጠቀስ ነው፡፡ ቢሮው በየጊዜው አዳጊ ከሆኑ ተግባራት በመነሳት የሰው ሃይል የማሟላት ስራ እየተሰራ ነው፡፡

ከአደረጃጀት አኳያ ከላይ በጥንካሬ የተገለጹት እንዳለ ሆኖ የተቋሙ አደረጃጀት ወረዳ ላይ ተንጠልጥሎ የቀረና በየቀበሌው የሚገነቡ የመስኖ አውታር ግንባታዎችን፤የመስኖ ተጠቃሚ ማኅበራትን በዘላቂነት እየደገፈ የተጠናከረ የመረጃ ሥርዓት አለመፈጠሩ ሠፊ የአሠራር ክፍተት እየፈጠረ ያለ ችግር መሆኑን ማጤን ተገቢ ነው፡፡

አሁን ያለውን የቢሮ አደረጃጀት፤ የሥራ ስፋትና የሰው ኃይል ብዛት እና ከሚያንቀሳቅሰው ሀብት ጋር ተከትሎ አስተዳደራዊ የሥራ ዘርፎች በተለይም የፋይናንስ ፤ ግዥና ንብረት አስተዳደር ፤ የሰው ሃይል ልማት እንዲሁም ዕቅድ ዝግጅት፤ክትትልና ግምገማ የሥራ ዘርፎች በአደረጃጀትም ሆነ አቅምን አጠናክሮ የተቋሙ ማዕከል መሆናቸውን ተገንዝቦ አደረጃጀቱን ለማስተካከል የተደረገውው ትኩረት በጣም አበረታች ነው፡፡

ክልሉ ካለው ሠፊ ሊለማ የሚችል መሬት እና የውኃ ሀብት ዕምቅ አቅም አንፃር አሁን ላይ በዘመናዊ መንገድ በመስኖ መልማት ያለበት መሬት እየለማ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም

የተገነቡት የዘመናዊ መስኖ ፕሮጀክቶች በቁጥር አነስተኛ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ የመስኖ ውኃ አጠቃቀምን ዘመናዊ በማድረግ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑና ገበያ ተኮር የሆኑ ምርቶችን በማምረት በሚፈለገው ደረጃ ማሳደግ አልተቻለም፡፡

በአጠቃላይ ተቋሙ በየጊዜው የሚሰጡት ወይም የሚጨመሩትን ተግባርና ኃላፊነቶች መሠረት በማድረግ ከዚህ ቀደም ምንም ያልታዩና የተረሱ እና ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸውን አደረጃጀቶች እየፈተሹ በጥሞና ይዞ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡

**መ. ከአሠራር አኳያ**

ተግባራትን ከላይ እስከ ታች ወጥነት ባለው መልኩ ተጠያቂነተንና ግልጸኝነትን በማስፈን እና ቅልጥፍናን በሚጨምር መንገድ ለመፈጸም በቢሮ በኩል አዋጅና ደንቦችን መሠረት ያደረጉ የተለያዩ መመሪያዎች ወጥተው ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቢሮው የራሱን የውስጥ አሰራር መመሪያ አዘጋጅቶ እየተገበረ ይገኛል፡፡

የመስኖ ፕሮጀክት ግንባታዎችን በተያዘላቸው ጊዜ፤ ወጪ እና ጥራት ለማጠናቀቅ ከክልሉ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ እና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር የተቋራጮች የአፈፃፀም መመዘኛ መመሪያ በማዘጋጀት ወደ ሥራ ተገብቶ እየተሰራበት የነበረ ሲሆን ይህም እንዲቀጥል ተደረጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከቢሮው ጋር አብረው ከሚሰሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ተቋራጮች እንዲሁም አማካሪዎች ጋር በተደረሰ ስምምነት መሰረት የአሰራር መርህ በማስቀመጥ በመስኖ ፕሮጀክት ጥናትና ዲዛይን እንዲሁም የግንባታ አፈጻጸም ላይ ወርሃዊ የሦስትዮሽ ስብሰባዎች እየተደረጉ ያሉ ሲሆን ይህ አሰራር ችግር ፈቺ በሆነ መልኩ ለወደፊቱም የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ስለሆነም በተቋራጮች እና አማካሪዎች ላይ የአስተሳሰብ እና የተግባር መሻሻሎች ታይተዋል፤ የውድድር መንፈስ በመንግስት የልማት ድርጅቶችም ሆነ በግል ተቋራጮች እና አማካሪዎች በኩል እየዳበረ መጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም በመንግስት የልማት ድርጅቶች፤የግል ተቋራጮች እና ኢንተርፕራይዞች ግንባታዎችን በውል አስተዳደር በተያዘላቸው ጊዜ፤ በተመደበላቸው በጀትና በጥራት አጠናቆ ለተጠቃሚ ኅብረተብ ማስረከብ ከፍተኛ ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህም በኅብረተቡ ዘንድ የመንግስትን ተዓማኒነት አሳጥቷል፡፡ ስለዚህ ይህ ችግር የተቋሙን መልካም ሥራዎች ጭምር ይዞ የሚጠፋ በመሆኑ በትኩረትና ጊዜ ሳይሰጠው የሚሰራ ተግባር ይሆናል፡፡

በተመሳሳይ  የመስኖ ውኃ ተጠቃሚ ማኅበራት ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ መሠረት በማድረግ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት የአደረጃጀት መመሪያ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ይሁን እና ለውኃው ሴክተር አመራሮች እና ባለሞያዎች እንዲሁም ለግብርና ሴክተሩ ባለሙያዎች  በመመሪያው ላይ እውቅና የተፈጠረ ቢሆንም በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት የመስኖ አውታሩን በዘላቂነት ሀብት እየፈጠሩ በባለቤትነት ይዞ ለመጠቀም የሚያስችል የተቀናጀ ሠፊ አቅም ግንባታ ሥራ እንደሚያስፈልግ በመገንዘብ የተጀመረውን ሥራ ማጠናከር ይጠይቃል፡፡

በዲዛይን ጥራት ጉድለት እና በአካባቢ ተጽዕና እንዲሁም በማኅበራዊ ጉዳዮች የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቀነስ ዲዛይኖች ወደ ግንባታ ከመግባታቸው በፊት ሁሉንም የሙያ ስብጥር ያሟላ መሆኑ ተረጋግጦ በባለሙያዎች በተናጠልና በጋራ ክለሳ በማድረግ  የተሰራው ዲዛይን በተጨባጭ መሬት ላይ መግጠሙን የማረጋገጥ ሥራ መሠራት እንዳለበት አሰራሮች ተዘርግተዋል፡፡ ይህ አሠራር ቀጣይነትና ወጥነት ባለው መንገድ መፈጸም ከተቻለ መሬት ላይ የሚፈጠረውን የዲዛይን ጥራት፤የአካባቢ ተጽዕኖ እንዲሁም ማኅበራዊ ችግሮችን መቀነስ ይቻላል፡፡ስለዚህ ሁሉም ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ ከመግባታቸው በፊት ይህ አሠራር ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል፡፡

በአጠቃላይ የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባሮቻችን በተገቢው መንገድ ለመፈጸም የተደረገው ጥረት  አበረታች ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ይህን እንቅስቃሴ በተፈለገው አግባብ መሬት የማስነካትና ተከታትሎ አፈጻጸሙን እየገመገሙ የማስተካከያ እርምጃዎችን በመውሰድ ረገድ እጥረቶች እንደነበሩ በመገንዘብ የተጀመረውን የአሠራር ሥርዓት አዳጊ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

### ሠ. ከግብዓት አቅርቦት አኳያ

ከቢሮ ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ  በወቅቱ የግንባታ ቁሳቁስ ያለማቅረብ ፤ እንዲሁም በክልል ደረጃ በጨረታ ሂደት ላይ መጓተት ሙሉ ለሙሉ ያልተቀረፈና ወደሚቀጥለው የእቅድ ዘመን ተሻግሮ የመጣ ችግር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ምክንያት የሚፈጠረውን የግንባታ መጓተት ችግር ለመቀረፍ በቅድመ ዝግጅት ምዕራፎች ሁሉም ወረዳና ዞን በትኩረት ይዞ እንዲቀሳቀስ ማድረግ፡፡

በአገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ የነበረውን የቁፋሮ ማሽን እጥረት ለመቅረፍ የክልሉ መንግስት በመደበው በጀት እስከ 500 ሜትር ጥልቀት ድረስ የሚቆፍሩ ሪግ ማሽኖችን፤ ክሬን ትራኮችና

ሌሎችን በመግዛት ከዚህ በፊት በአማራ ውኃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ስር በአንድ ክፍል ውስጥ የነበረውን የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ቡድን ራሱን ችሎ ኢንተርፕራይዝ እንዲሆን በማድረግ በክልሉ ብሎም በአገር አቀፍ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት ተችሏል፡፡

የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ 2014 ዓ.ም የተቋቋመ ቢሆንም በአዲስ ለተቋቋሙ ዞኖች ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ፕሪንተሮች እንዲሁም ላፕቶፖች እንዲሰራጩ የተደረጉ ሲሆን በተጨማሪም በጣና በለስ የቆላ ስንዴ ልማት ተደራጅተው በግብርናው ዘርፍ ለተሰማሩ ወጣቶች ለመስኖ ሥራ አጋዥ የሚሆኑ ሁለት ትራክተሮች ከመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በስጦታ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ በትግራይ ወራሪ ኃይል በተቀሰቀሰው ጦርነት ምክንያት ለቆቦ ጊራና አትክልትና ፍራፍሬ ልማት አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ፓምፖችንና ጄኔሬተሮች ላይ ጉዳት በማድረሳቸው አትክልትና ፍራፍሬው እንዳይደርቅ ሁለት ጀኔሬተሮችን ቢሮው ገዝቶ የመስኖ ልማቱን ለመታደግ ተሞክሯል፡፡

የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ራሱን ችሎ ሲወጣ ከውኃና ኢነርጂ ቢሮ ንብረት ክፍፍል ሲደረግ ለቢሯችን 13 ተሽከርካሪዎች የተመደቡ ቢሆንም በዞንና በወረዳ ደረጃ የተሽከርካሪና ሌሎች ሀብቶች ክፍፍል እንደታሰበው ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም፡፡

የበጀት ምደባን በሚመለከት ለቢሮው ከበመደበኛ፣ በዘላቂ ልማት ግብ እየተመደበለት እየተንቀሳቀሰ ሲሆን አቅም በፈቀደ መጠን ለመሥራት ቢሞከርም ከፍተኛ የሆነ የግብዓት አቅርቦት ችግር በተለይ ዞኖችና ወረዳዎች በተሽከርካሪ እና በቢሮ መገልገያ መሳሪያዎች እጥረት እየተቸገሩ መሆኑ ተገምግሟል፡፡ በዚህ ምክንያት እና ወቅቱ በፈጠረው የጸጥታ ችግር በካፒታል በጀት የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን በተገቢው መንገድ ለመደገፍና ለመከታተል ሳይቻል በመቅረቱ የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ሳይጠናቀቁ ቀርተዋል፡፡

በተመሳሳይ ሴክተሩ አዲስ በመሆኑና ከፍተኛ ግብዓት የሚጠቀም ሴክትር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንዲሁም የዞንና የወረዳ መዋቅር በአዲስ የተከፈተ በመሆኑና የመስኖ ተቋማት ከወረዳ ማዕከል የራቁ በመሆናቸው ለትራንስፖርት አገልግሎት ምቹ ባለመሆናቸው ችግሩን ለመፍታትና አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ በቀጣይ የተሽከርካሪ አቅርቦት ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ይሆናል፡፡

### 4.1.2. የአበይት ተግባራት አፈጻፀም

በየዓመቱ አዳጊ የሆነ የመስኖ መሰረተ ልማት ግንባታ ቢኖርም በአስፈጻሚ አካሉ፣ በአማካሪዎች እና፣በተቋራጮች የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ውስንነት የመስኖ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ፣በጀትና ጥራት ተጠናቀው ወደ ልማት ባለመግባታቸው ምክንያት ዝቅተኛ አፈጻጸም እንዳለው ያመላክታል፡፡ ስለዚህ በ10 ዓመቱ የመጀመሪያው አምስት ዓመታት የዕቅድ ዘመን የታዩ ጉድለቶችን በማረም የተጀመሩ እና አዲስ የመስኖ መሰረተ ልማት ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ ወደ ልማት ማስገባት የተጀመረውን ጥረት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ እየተሰራ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በክልሉ ያለውን የውኃ ሀብት ለመስኖ አገልግሎት በማዋል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የዘመናዊ መስኖ አውታሮች ግንባታ በስፋት እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በመሆኑም አሳታፊ የመስኖ ጥናት ዲዛይን ሥራዎችን በማካሄድ የክልሉን ኅብረተብ የዘመናዊ መስኖ ልማት ተጠቃሚ ለማድረግ ባሳለፍነው 2014 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 97,356 ሄ/ር የሚሸፍኑ 427 ፕሮጀክቶች በመነሳት የ3 ዓመታት እቅድ ዘመን 60,564 ሄክታር የሚሸፍኑ 366 ፕሮጀክቶችን (354 አነስተኛ እና 12 መካከለኛ) በማከናወን ወደ 157,920 ሄክታር (793 ፕሮጀክቶች) ለማሳደግ ታቅዶ የነበረ ሲሆን፣ በአጠቃላይ እስከ 2017 ዓ/ም መጨረሻ 140,850 ሄክታር መሬት የሚያለሙ 793 አነስተኛና መካከለኛ የመስኖ ፕሮጀክቶችን የጥናትና ዲዛይን ሥራ ተከናውኗል፡፡

የመስኖ ግንባታ ሥራዎችን በማካሄድ የክልሉን ኅብረተብ የዘመናዊ መስኖ ልማት ተጠቃሚ ለማድረግ በ2014 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 221,959 ሄ/ር የሚሸፍኑ (5,721 ፕሮጀክቶች) በመነሳት የ3 ዓመታት እቅድ ዘመን 91,860 ሄክታር የሚሸፍኑ 960 ፕሮጀክቶችን (720 አነስተኛ እና 240 መካከለኛ) በማከናወን ወደ 313,819 ሄክታር (6,681 ፕሮጀክቶች) ለማሳደግ ታቅዶ የነበረ ሲሆን በአጠቃላይ እስከ 2017 ዓ/ም መጨረሻ 261,334 ሄክታር መሬት የሚያለሙ 6,185 (4,646 አነስተኛና 1,539 መካከለኛ) የመስኖ ፕሮጀክቶችን የግንባታ ሥራዎችን ማከናወን ተችሏል፡፡

በክልላችን በፌደራል በጀት ጥናትና ዲዛይናቸዉ እየተሰሩ ያሉ 183,000 ሄ/ር የሚያለሙ 5 ከፍተኛ ፕሮጀክቶች በጅምር ያሉና በተለያዩ ምክንያቶች ለረጅም ዓመታታ ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ሲሆኑ በቀጣዩ 5 ዓመታት በትኩረት በመያዝ ተጠናቀው ወደ ግንባታ እንዲገቡ ይሰራል፡፡ እንዲሁም 22,310 ሄ/ር የሚያለሙ 7 ከፍተኛ ፕሮጀክቶች ግንባታ በጅምር ያሉና በተለያዩ ምክንያቶች ለረጅም ዓመታት ተጠናቀው ወደ ልማት ካለመግባታቸው በላይ የመልካም

አስተዳደር ችግሮች እየሆኑ የመጡ ፕሮጀክቶች ሲሆኑ በቀጣዩ 5 ዓመታት በትኩረት በመያዝ ተጠናቀው ወደ ልማት እንዲገቡ ይሰራል፡፡ እነዚህ የመስኖ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸዉ የግንባታ ጊዜና በጀት ባለመጠናቀቃቸዉ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ አልተቻለም፡፡ ስለዚህ የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ለማሻሻል በሚኒስቴር መስሪያቤቱና በክልሉ ፈጻሚ አካት መካከል የተናበበ ቅንጅታዊ አሰራር መኖር እንዳለበት ያመለክታል፡፡

ግንባታቸው የተጠናቀቁ የመስኖ መሰረተ ልማቶች ዘለቄታቸዉ እንዲረጋገጥና የታሰበውን ልማት ለማምጣት የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎችን ማህበር በማደራጀትና በማጠናከር የመስኖ ተቋማት ተቋማዊ አሰራር እንዲኖራቸዉ ማድረግ ዋና ተግባር ነው፡፡ በዚህም መሰረት  የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበርን ማቋቋምን በሚመለከት በ2014 ዓ.ም ከነበረው  939 አፈፃፀም ላይ 675 የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበርን በማቋቋም በ2017 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 1,614 ማህበራት ለማሳደግ ታቅዶ የነበረ ሲሆን በአጠቃላይ እስከ 2017 ዓ/ም መጨረሻ 1,600 የመስኖ ተቋማት የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ማቋቋም ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በመስኖ ልማት ዘርፍ በየደረጃው የታዩ ችግሮችን በማየት እና ከእነዚህም ቸግሮች ሊያወጣ የሚችል ዘዴ በመስኖ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን፤ግንባታና ክትትል እና ተቋማት አስዳደርንና አጠቃላይ በመስኖ ልማት ዘርፍ ያለዉን የአቅም ውስንነት በቀጣይ አስተተካክሉ ስትራቴጂክ አቅጣጫዎችን ያመላከተ ዕቅድ ነድፎ ስራን፣ ጊዜንና ሀብትን በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል እንዲሁም የኀብረተቡን አሳታፊነትና ዘለቄታዊ ተጠቃሚነትን ያረጋገጠ ልማት ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

## 4.2 በአገር አቀፍ ደረጃ የመስኖ ዘርፍ ዕቅድ እንደ መነሻ

በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በታቀደው የ10 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ መሠረት በአገር አቀፍ ደረጃ የመስኖ ጥናትና ዲዛይን ሥራዎች በ2012 ዓ.ም ከተደረሰበት 600,000 ሄክታር በመነሳት በ2022 ዓ.ም 1.6 ሚሊዮን ሄክታር ለማድረስ እና በግንባታው ዘርፍም በ2012 ዓ.ም ከተደረሰበት 490,000 ሄክታር በ2022 ዓ.ም 990,000 ሄክታር ለማድረስ ታቅደል፡፡

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በኩል የግንባታ ውል የተወሰደባቸው የማልማት አቅማቸው 50,578 ሄክታር መሬት የሆኑ በክልላችን የተጀመሩና ያልተጠናቀቁ 5 ከፍተኛ ዘመናዊ የመስኖ ፕሮጀክቶች (ላይኛው ርብ፣ ታችኛዉ ርብ፣ አጅማ ጫጫ፣ መገጭና ጣና በለስ) ተጠናቀው ወደ ልማት እንደሚገቡ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሚንስትር መስሪያቤቱ በጀት በቁጥር

6 የሚደርሱ (ሽንፋ፤ አንገረብ፣ ትርካን፣ አይማ ግድብን አይማ ቀኝ ፣መቻላና ተላ) የማልማት አቅማቸው 192,500 **ሄክታር** መሬት የሆነ ከፍተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ስራቸው ካለቀ በኋላ ተገንብተው ወደ ልማት እንደሚገቡ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ በመስኖ ልማት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ የሚሆኑ ምርቶችን በማምረት ለኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ዋነኛው ጉዳይ ዘመናዊ መስኖን ማስፋፋት በአገር አቀፍ ደረጃ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

## 4.3 በዓለም አቀፍ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የዘላቂ ልማት ግቦች እንደ መነሻ

### 4.3.1 የዘላቂ ልማት ግቦች

የዘላቂ ልማት ግቦች እ.አ.አ. በ2015 በሁሉም የተባበሩት መንግስታት አባል ሃገራት ድህነትን ለማጥፋት፣ተፈጥሮን ለመጠበቅና ሁሉም የሰው ልጆች እ.አ.አ. እስከ 2030 ድረስ ሠላምንና ብልጽግናን እንዲያረጋግጡ እንደ ሁለንተናዊ ጥሪ የተቀበሉት ሰነድ ነው፡፡ ይህ ሰነድ ዓለማችንን በመጠበቅ ብልጽግናን ለማስፋፋትና የተቀራረበ ኢኮኖሚ እንዲገነባ የሁሉም ሃገሮች የድርጊት መርሀግብር ሆኖ ጸድቋል፡፡ የዘላቂ ልማት ግቦች በአንድ አካባቢ የሚደረጉ እርምጃዎች በሌሎች ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳርፍ በሚያሳይ መልኩ በቅንጅትና በመስተጋብር የተቀረጹ ናቸው፡፡

ይህ የልማት አጀንዳ የማይነጣጠሉና ሁሉን አቀፍ ባህሪያት ያሏቸው 17 የዘላቂ ልማት ግቦች ያሉት ሲሆኑ የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ስልታዊ እቅድ ከነእዚህ የዘላቂ ልማት ግቦች አንጻር እንዲቃኝ በማድረግ ይሰራል፡፡ በዋናነትም ጤናማ ኅብረተብ ለመፍጠር፣ ድህነትን ማጥፋት፣ ርሃብን ማስወገድ፣ ዘላቂ የመስኖ ውኃ አቅርቦት፤ የፆታ እኩልነትን ማስፈን፣ ምቹ የሥራ ቦታንና ሁሉን አቀፍ የኢኮኖሚ እድገትን ማምጣት፣የሥራ እድል ፈጠራን ማበረታታት፣ አረንጓዴ ልማትን መደገፍ እና አካባቢያዊ ሥነ ምህዳርን መጠበቅ ያስፈልግል፡፡

በዚህ መነሻነት የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ከባቢያዊ ስነምዳርን ያገናዘቡ የጥናትና ዲዛይን፣ግንባታ፣የመስኖ ተቋማት አጠቃቀም አስተዳደርና ጥገና ሥራዎችን እና የቆላማ አካባቢዎች ልማት ተገቢውን የጥራት መቆጣጠሪያ ስልት በመከተል ለግቦቹ መሳካት አበክሮ ይሠራል፡፡

### 4.3.2 የአጀንዳ 2063 ግቦች

በዘላቂ ልማት አጀንዳ 2030 ዝግጅት ወቅትና ድርድሮች ላይ የአፍሪካ ህብረት 2063 አጀንዳ ተቀባይነት እንዲኖረው ተፅዕኖ መፍጠር የቻለ መሆኑ ይታወቃል፡፡በዚህም 17ቱ የዘላቂ ልማት ግቦች ከአፍሪካ አጀንዳ 2063 ውስጥ ካሉ 20 ግቦች ጋር ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም የዘላቂ የልማት ግቦችን ከአሥር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ጋር እንዲተሳሰሩ ሲደረግ የአፍሪካ ህብረት አጀንዳ 2063ም እንደተሳሰረ መታወቅ አለበት፡፡ አጀንዳ 2063*" የምንፈልጋትን አፍሪካ* " በሚል መሪ ሐሳብ አህጉሩ ለ50 ዓመት (እ.አ.አ ከ 2013 እስከ 2063) የሚመራበትን እቅድ የያዘ ማዕቀፍ ነው፡፡

## 4.4 ሀገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች እንደ መነሻ

የቢሮውን መሪ ዕቅድ በታሰበው መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ፖሊሲዎችና የህግ ድጋፎች በግልጽ ማመልከት ያስፈልጋል፤ በዚህም መሠረት ለቀጣይ አምስት ዓመታት ለሚዘጋጀው መሪ ዕቅድ እንደመነሻ የሚከተሉት ፖሊሲዎችና ስተራቴጅዎች ተለይተዋል፡፡

### 4.4.1 የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፡

የግብርናና ገጠር ልማቱ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ዕድገት እንዲያስመዘግብ ለሚያደርገው ጥረት ቢሮው ለክልላችን አጠቃላይ ለምርት ዕድገት አስተዋፅዖ የሚያደርጉ የመስኖ አውታሮችን በተፈለገው ጊዜና በተመጣጣኝ ዋጋ ግንባታ በመፈጸም ለዘርፉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፤ የቀጣይ ስምንት ዓመታት የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የመስኖ አቅምን በማጎልበት ግብርናውን ከዝናብ ጥገኝነት ማላቀቅ፤ የሜካናይዜሽን አገልግሎትን ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ሥራ መሆን ይገባዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ካስቀመጣቸው የሃያ ዓመታት ግቦች መካከል የግብርና መር የኢኮኖሚያዊ እድገትን በማሳለጥ ወደ ኢንዱስትሪ መር የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ማድረግ አንዱና ዋናው ትኩረት ነው፡፡ ይህን ለመፈጸምም የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ተቀርጿል፡፡ የግብርናው ዘርፍ ለአብዛኛው የሃገራችን የሰው ኃይል የሥራ መስክ ሲሆን፣ ከሃገሪቱ አጠቃላይ ምርት ቀዳሚውን ድርሻ ይሸፍናል፡፡

### 4.4.2 የማስፈጸም አቅም ግንባታ ስትራቴጂና ፕሮግራሞች፤

የማስፈጸም አቅም ግንባታ፣ የአደረጃጀት፣ አሠራርና የሰው ኃይል ጥምረትና መስተጋብር እንዲኖር ማስቻል በሚደረገው ጥረት ቢሮው በህግ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመወጣት በሁሉም ደረጃ የሚገኙ ኃላፊዎችና ፈጻሚዎች አቅም በተከታታይ መገንባት፣ የተለያዩ የአሠራር ማሻሻያ ሀሳቦችን በማጥናት ማስወሰን እና ተግባራዊ ማድረግ፣ በመስኖ ግንባታና በመስኖ ልማት አጠቃቀምና አስተዳደር ዙሪያ የምክርና ድጋፍ ሥራዎችን አጠናክሮ መሥራትና በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ እና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠትን ያካትታል፡፡

### 4.4.3 የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ

ለአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ ተፈጻሚነት ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በሚደረገው ርብርብ የሚገዙ ንብረቶች የኢትዮጵያን ስታንዳርድ ያሚሉና በሚገነቡ የመስኖ አውታሮች የሚለሙ ቋሚና ሌሎች አረንጓዴ ተክሎች ለአካባቢ ተስማሚነት ዋነኛ መሳሪያዎች በመሆናቸው እነዚህን አጠናክሮ በማስቀጠል ለአከባቢ ጥበቃ አጋዥ የሆኑ ተግባራትን መፈፀም፡፡ የሚገነቡ የመስኖ ተቋማት አካባቢን የማይጎዱ መሆናቸውን በማረጋገጥና የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ማረጋገጫ የይሁንታ ፈቃድ እንዲያገኙ ሥራዎች ይሰራሉ፡፡

### 4.4.4 የመስኖ ጥናትና ዲዛይን፣ግንባታ እና ተቋማት አስተዳደር ማስፈጸሚያ መመሪያዎች

የክልሉን አስፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነትለመወሰን በወጣው አዋጅ መሰረት የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ በክልላችን ያለውን በመስኖ የሚለማ መሬት ወደ ልማት በማስገባት በክልላችን ብሎም በሀገራችን ያለውን የምግብ ሰብል ምርት እጥረት መቀነስና ለወጣቶች ሠፊ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚል ጥቅል አላማ ለማስፈጸም ትልቅ ኃላፊነት ተሰቶታል፡፡

### 4.4.5 የመስኖ ግዥ አፈጻጸምና የንብረት አስተዳደር መመሪያዎች፤

ግዥዎች በምን አግባብ መከናወን እንዳለባቸው ማስጨበጥ፤ ንብረቶችን ከብክነት በጠበቀ መልኩ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል፤በግዥ ሥርዓቱ ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን የግዥ አፈጻጸምና የንብረት አስተዳደር መመሪያው በሚያስቀምጠው አግባብ የመፍትሄ ሀሳቦችን በማስቀመጥ መተግበር ያስፈልጋል፡፡

የግዥና የንብረት አስተዳደር መመሪያዎችን በዕዉቀት ላይ የተመሰረተ በማድረግ የተቋራጮችን የአማካሪዎችን እና የባለድርሻ አካላትን አቅም በማሳደግ አጠቃላይ የክልሉን የመስኖ ዘርፍ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም በሚያሻሽል አግባብ መቃኘት ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የዘረዘርናቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጅዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መውጣት የክልላችንን ልማትና ዲሞክራሲ በግልፅ በተቀመጠ አቅጣጫ ላይ እንዲመራ ያደርገዋል። ቢሮውም የኅብረተቡን ፍላጎት ለማሟላትና ለማረጋገጥ ከተቋቋመ የክልል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አንዱ እንደመሆኑ መጠን ቀልጣፋ፣ ውጤታማና የላቀ አገልግሎት በመስጠት በግልፅ አቅጣጫ ላይ የተመሠረተ ተግባር እንዲያከናውን የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ይፈጥርለታል፡፡

## 4.5 አገራዊና ክልላዊ ራዕይ እንደመነሻ

አገራችን በኢኮኖሚው መስክ በ2017 መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ የማሰለፍ ራዕይ ተቀርጾና መግባባት ላይ ተደርሶበት ይህን ራዕይ እውን ለማድግ ርብርብ እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከዚህ በመነሳት እና ይህን የተጀመረ እንቅስቃሴ በማጠናከር በ2022 በረዥም ጊዜ የእቅድ ዘመን እንደሀገር ለማሳካት የተቀረፀውን ራዕይ ለማሳካት ቢሮው የሚከተሉትን አገራዊና ክልላዊ ርዕዮችን እንደመነሻ ተጠቅሟል፡፡

- **ሀገራዊ ርዕይ፡-** **በ2022** ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት ማድረግ፡፡
- **የክልሉ ራዕይ፡-** ክልሉ ከነበረበት ኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታና የመልማት አቅም እንዲሁም ወደፊት ሊደርስበት ከሚገባው ዕድገት ደረጃና በአገር ግንባታ ሊኖረው ከሚገባው ሚና አንጻር በመገምገም “ሠላምና አንድነቱ የተጠበቀ፣ የህዝብ ተጠቃሚነትና አካታችነት ባረጋገጠ መልኩ ጠንካራና የዳበረ ኢኮኖሚ የገነባ፣ድህነትን ትርጉም ባለው ሁኔታ የቀነሰ፣ ከአቻ ክልሎች ጋር በጠንካራ ትብብር፣ መደጋገፍና ወንድማማችነት መንፈስ የሚኖር እንዲሁም ለአገራዊ አንድነትና ብልጽግና በማበርከት ረገድ ወሳኝ ሚና ያለው ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ላይ የደረሰ ክልል መፍጠር”

## 4.6 ለዘርፉ ወሳኝ የሆኑ ሀብቶች እንደመነሻ

### ሀ. የዉሃ ሀብት

ክልሉ በአጠቃላይ 44.8 ቢሊዮን ሜትር ኩብ የገጸምድር ውኃና ሰፊ የከርሰ ምድር ውኃ ባለቤት ሲሆን ከተፋሰሶች ዉስጥም የአባይ ተፋሰስ 60.46% ፤የተከዜ ተፋሰስ 27.56%፤ የአዋሽ ተፋሰስ 10.22%፤ እና የጎሉና /ደረቅ ተፋሰስ/ 1.76% የክልሉን ስፋት ይሸፍናሉ፡፡ በአራቱም ተፋሰሶች ውስጥ የሚገኘው የወንዞች አማካይ አመታዊ ፍሰት 45 ቢሉዬን ሜትር ኩብ እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ክልሉ ከወንዞች በተጨማሪም ስፋት ያላቸው ሀይቆችና የከርሰ ምድር ውሀ ሀብት እንዳለው ይገመታል፡፡

ይሁን እንጅ ከላይ የተገለፀው የውሀ ሀብት ክምችት ቢኖርም ይህን እምቅ ሀብት አልምቶ የምግብ ዋስትናን በሚያረጋግጥና ድህነትን በሚያስወግድ መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የተጀመረዉ እንቅስቃሴ አበረታች ቢሆንም ከሚፈለገዉ ደረጃ ላይ የደረሰ ግን አይደለም፡፡ በመሆኑም የተጀመረዉን እንቅስቃሴ የበለጠ በማጠናከር የምግብ ሉአላዊነትን ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ለገበያ ተፈሊጊ የሆኑ እና ለኢንደስትሪ ግብዓት የሚሆኑ የግብርና ምርቶችን ለማምረት ዘመናዊ መስኖ ፕሮጀክቶችን በማስፋፋት መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ ሀገሮች ተርታ ሊያሰልፍ የሚያስችል ስራ መስራት ይጠበቃል፡፡

### ለ. በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት

የአማራ ብሄራዊ ክልል 157,126.83 ስኩዬር ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት ሲኖረው ከዚህም ውስጥ በመስኖ ሊለማ የሚችለው መሬት 2.2 ሚሊዮን ሄክታር መሬት፤በመስኖ መልማት የሚችል በሚል ተለይቷል፡፡

ከዚህ አንጻር የዘርፉን አፈፃፀም በማሻሻል የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል። ይህም ተግባራዊ የሚሆነው ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ፕሮጀክቶች ለይቶ መገንባትና ከዚህ በፊት የተጠኑና ወደ ሥራ ያልገቡ ፕሮጀክቶችን ጥናትና ዲዛይን ገምግሞ ወደ ግንባታ ማስገባትና የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም ማሳደግ በቀጣይ ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት ይሆናሉ::

የአነስተኛ መስኖ መሰረተ ልማት የማስፋፋት ስራን በተሳካ ሁኔታ ተጀምሮ እየሰፋ የመጣና የቆዬ የህብረተሰብ ጥያቄን የመለሰ ቢሆንም አሁንም በርካታ የሆነ የክልላችን አካባቢዎች የመስኖ አውታር ግንባታ ስራ ያልተሰራባቸዉና የህብረተሰቡ ጥያቄዎችም ከጊዜ ወደ ጊዘ

እየጨመረ መጥቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሰፋፊና ምርታማ የሆኑ መሬቶችን በመስኖ ማልማት ሲቻል በበጀት እጥረትና በተቋማዊ አቅም ውስንነት የተነሳ የታሰበውን ያህል ማከናወን አልተቻለም፡፡ በሌላ በኩል ተገንብተው ያለቁና ለመስኖ ውሀ ተጠቃሚ ማህበራት የተላለፉ የመስኖ አውታሮችም ብዙ አገልግሎት ሳይሰጡ የሚበላሹ በመኖራቸዉ ዉጤታማ የአሰራር ስርአቶችን በመዘርጋትና ተቋማዊ ለውጥና ጥንካሬ በመፍጠር ችግሩን በዘላቂነት መፍታት አስፈላጊ ነው፡፡

በዝናብ እጥረት ምክንያት የሚመጣው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ችግር ውስብስብ ከመሆኑ አንጻር በሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመፍታት የመስኖ ስራን የርብርብ ማዕከል አድርጎ ማስቀጠል አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ በፊት በአነስተኛ መስኖ መሰረተ ልማት ረገድ የተገኙ መልካም ልምዶችን በመቀመር እጥረቶችን ደግሞ በአግባቡ በመገምገም በፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት አሁንም ያልተፈቱ የአመለካከትና የክህሎት ክፍተቶች በመለየት በተከታታይ ውይይቶችና ሙያዊ ስልጠናዎች እንዲፈቱ በማድረግ የመስኖ መሰረተ ልማት ስራዎች በሚቀጥሉት ስምንት አመታትም ከፍተኛ የትኩረት ማዕከል ሆኖ ይቀጥላል፡፡

## ሐ. የተቋሙ የቴክኖሎጅ አቅም

ቢሮው ከተቋቋመ ጀምሮ ተግባራቱን ለማከናወን እንዲረዳው ዴስክ ቶፕና ላብቶፕ ኮምፒተሮችን እና ሌሎች የቴክኖሎጅ ውጤቶችን በመጠቀም እየሰራ በተለያዩ የህዝብ ግንኙነት ተግባራት የቢሮውን እንቅስቃሴ ለተገልጋዮች ተደራሽ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ የተቋሙን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ የአገልግሎቱ ኢሜልና የፌስ ቡክ ገጽ በመክፈት እየተሰራ ይገኛል፡፡ የበጀት፣የሂሳብና ኦዲት እንቅስቃሴዎችን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የአይቤክስ ቴክኖሎጅ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የአብክመ መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ተቋቁሞ በ2014 ዓ.ም ወደ ሥራ ሲገባ አዲስ ከመሆኑ አንጻር በተሟላ ሁኔታ ቁሳዊ ሀብቶች ሳይሟሉ በተወሰኑ የቢሮ መገልገያዎችና ዕቃዎች በመጠቀም እየተንቀሳቀሰ የቆየ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በኪራይ ህንጻ፣ 16 ተሽከርካሪዎችን ጨምሮ ምንም እንኳን በቂ ባይሆንም ስራውን ሊያሰራ የሚችል የቢሮ መገልገያዎችና ፈርኒቸሮች ከሞላ ጎደል ተሟልተው ትግባራት በተያዘላቸው ጊዜና ሁኔታ እተከናወኑ ይገኛል፡፡ በሚቀጥሉት ዓመታት የመስኖ ተቋማት የተገነቡበትን ዓ/ም፣የሚያለሙትን የመሬት መጠንና ምርታማነት፣ አገልግሎት የሚያገኘዉ የህብረተሰብ ቁጥር እንዲሁም

ከተቋሙ ጋር የሚያያዙ ሁሉንም መረጃዎች በማሰባሰብ መረጃዎችን በአንድ ቋት በመሰብሰብ፤ በማደራጀትና በማሰራጨት የመረጃ ልዉዉጡን ከማሳለጥም በተጨማሪ በየጊዜዉ የሚቀያየረዉን መረጃ በእዉነት ላይ የተመሰረተና አስተማማኝ እንዲሆን ለማድረግ ይሰራል፡፡

### መ. የሰው ሀብት

በክልላችን ለስራ ዝግጁ የሆነና ሰፊ የማልማት የጉልበት አቅም ያለው ወንድ= 6,489,320 ሴት= 6,750,833 ድምር= 13,240,153 ለሥራ ዝግጁ የሆነ የሰው ሀብት የሚገኝበት ሲሆን ይህን ጉልበት ተጠቅሞ ወደ ልማት በማስገባት የክልላችን የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥና ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚሆኑ የእርሻ ጥሬ ዕቃዎችን ማምረትና ማቅረብ የግዴታ ውዴታ በመሆኑ ለአንድ ተቋም የሚተው ባለመሆኑና የሁሉም የርብርብ ማዕከል በመሆኑ ቢሯችንም የሚጠበቅበትን ድርሻ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡ የመስኖ ሥራው በክልል ከሚገኙ የዞንና የወረዳ ነዋሪዎች የሚመነጭ እንደመሆኑ እና ዘርፉ ለከፋ የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባር የተጋለጠ ከመሆኑ አኳያ ስራው በመጠን /ብዛት/ እና በዓይነት እጅግ ብዙ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም በቢሮው 133 በዞን 206 በወረዳ 2288 በአጠቃላይ 2,627 የሠው ኃይል እንደሚያስፈሌግ ታስቦ የተተራጀና ወደ ስራ የተገባ ሲሆን ከተፈቀዱ መደቦች በአጠቃላይ 1,363 (51.9%) እንዲሟላ ተደርጓል ፡

## 5. የትኩረት መስኮች

ቢሮው ያስቀመጠውን ራዕይ ከግቡ ለማድረስ የሚያስችሉ 5 የትኩረት መስኮች አዘጋጅቷል፡፡ እነዚህ የተዘጋጁ የትኩረት መስኮች የተቋሙን ክፍተቶች የዳሰሱ፤ከዲይሬክቶሬቶች ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖራቸውና የተቋሙን ሠራተኞች ሙሉ ትኩረት ለመሳብ እንዲችሉ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

| ተ.ቁ | የትኩረት መስክ | ውጤት |
|---|---|---|
| 1 | የክልሉን በመስኖ የመልማት አቅም ያገናዘበና አሳታፊ ጥናትና ዲዛይን መስራት፤ | ጥራቱን ጠብቆ የተዘጋጀ የጥናትና ዲዛይን ሰነድ፤ |
| 2 | የክልሉን የመስኖ መሰረተ ልማት ማስፋፋትና በቂ የመስኖ ውኃ ማቅረብ፤ | ለመስኖ ልማት የሚውል በቂ የመስኖ አውታር፤ |

| | | |
|---|---|---|
| 3 | የመስኖ ተቋማትን ዘላቂነት በሚያረጋግጥ ተቋማዊ አስተዳደር መፍጠር፤ | በዘላቂነት የሚያገለግሉ ሰፊ የመስኖ ተቋማት፤ |
| 4 | የቆላማ አካባቢዎችን ሁሉን አቀፍ ልማት ማስፋፋት፤ | ሁሉን አቀፍ ቆላማ አካባቢ ልማት፤ |

## 6. የዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች

የመስኖ ልማት የግብርና ዝመናን በማረጋገጥ በዘርፉ ምርትና ምታማነትን ለማሳደግ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት የመስኖ ልማትን በተመለከተ ግብርናን ለማዘመንና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተጀመሩ ጥረቶች ቢኖሩም ዘርፉን በሚፈለገው ደረጃ ከማሳደግ አኳያ ብዙ ሥራዎች ይቀራሉ። በመሆኑም በቀጣይ የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ የምግብ ሉዓላዊነትን በክልል ደረጃ ለማረጋገጥ እንዲሁም ለሌሎች ዘርፎች በበቂ ሁኔታ ግብዓት በሚሆን ደረጃ ለማድረስ መካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ አውታሮች ግንባታን በማካሄድ የመስኖ ልማትን ማስፋፋትና የግብርና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶት ይሠራል።

የመሠረተ ልማት አቅርቦትና ዝርጋታ በራሳቸው የሚኖራቸው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጠቀሜታ እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት በአካባቢዎች ላይ ያለውን እምቅ የመልማት አቅም በአግባቡና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ጥቅም ላይ በማዋል ለአካባቢውና ለአጠቃላይ ህብረተሰብ የሚኖረውን ፋይዳ ለማሳደግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል። ከዚህ አንጻር በቀጣይ 5 ዓመታት የሚገነቡ የመስኖ መሠረተ ልማቶች የልማት ኮሪደሮችን እምቅ አቅምን ማዕከል ያደረጉ እንዲሆኑ፣ የመስኖ ልማትን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የሚያስተሳስር ሥርዓት በመዘርጋት ቅንጅታዊ አሠራርን እውን ለማድረግ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል። የቀጣይ 5 ዓመታት የቢሮው መስኖ ልማት የትኩረት አቅጣጫዎች እንደሚከተለው ተለይተዋል፡

- የተቀናጀ የመስኖ ባለድርሻ አካላት ትስስር (Interconnectivity) መፍጠር፤
- የተቀናጀ የውሀ ሀብት ልማት አስተዳደር ተግባራዊ ማድረግ፤
- በክልላችን ያሉ የመስኖ ተቋማትን ለተደራጁ የአካባቢው ወጣቶች የስራ እድል መፍጠሪያ ማድረግ፤
- ሀገራዊና ክልላዊ ወቅታዊ ችግሮች ላይ ትልቅ ትኩረት አድርጎ የውሀና መስኖ ጥናት፣ ምርምርና ስልጠናን የሚያስተባብርና የሚመራ ጠንካራ ክልላዊ ተቋም ማቋቋም፤

- በክልሉ የሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞችን፣ የጥናት እና ምርምር ማዕከላትን፣ የግንባታ ስራ ተቋራጮችን በስብስብ (Clustering) ስርዓት መዘርጋትና ጠንካራ ሀገራዊና አለማቀፋዊ ግንኙነት መፍጠር፤
- የመስኖ ስራ አደረጃጀትና ትስስር ስርዓት ክልላዊውን የመስኖ ልማት ስርዓት በማዘመን ሀገር አቀፋዊ ቁመና ላይ ለማድረስ የሚያስችለን የአሰራር አቅጣጫዎች ተደርገው ተወስደዋል፡፡

# 7. የቢሮው የ5 ዓመታት ዕቅድ

## 7.1 የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ጥቅል ዓላማ፡

የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ዘላቂ የመስኖ ዉሀ እንዲኖር ማስቻል እና አጠቃቀሙን ዘመናዊ በማድረግ የግብርና ምርትና ምርታማነትን በመጨመር በክልሉ በቤተሰብ ደረጃ ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ብሎም ድህነትን ለመቀነስ የመስኖ ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጾ እንዲኖረዉ ማድረግ ፡፡

## 7.2 የቢሮው ግቦችና

- ❖ ጥናትና ዲዛይን የሚሰራላቸውን ፕሮጀክቶች ቁጥር በ2017 ከነበረበት 793 ወደ 1,408 በማሳደግ የሚለማውን መሬት ከ140,850 ሄ/ር ወደ 424,800 ሄ/ር ማስፋት ፤
- ❖ የሚገነቡ ፕሮጀክቶችን ቁጥር በ2017 ከነበረበት 6,148 ወደ 7,754 በማሳደግ ፤የሚለማውን መሬት ከ260,269 ሄ/ር ወደ 464,177 ሄ/ር ማስፋት ፤
- ❖ የሚቋቋሙ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎችን ማህበር ቁጥር በ2017 ከነበረበት 1,600 ወደ 7,754 ማሳደግ ፤
- ❖ የቆላማ አካባቢዎችን ሁሉን አቀፍ ልማት በማስፋፋት የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አፈጻጸሙን ከነበሩበት ወደ 10% ማሳደግ፤

# 8. የማስፈጸሚያ ስልቶች

የመስኖ ልማት ዓላማዎችና ግቦችን ለማሳካት በመስኖ ልማት ዙሪያ የመንግስት ወጪ ቅነሳና አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋት፣ተግባሮችን በቡድንና በጋራ እውቅና በመፈጸም የላቀ

ውጤት ማስመዝገብ፤ በቢሯችን ውስጥ ቁጠባን መሠረት ያደረገ የሀብት አጠቃቀምና አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት ለበለጠ ልማትና መልካም አስተዳደር መነሳሳት፤

የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች አሳታፊና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራና በትብብር መስራት፤ይህ በእንዲህ እንዳለ የፈጻሚውን የአመለካከትና የአቅም ግንባታ ሥራ ከፍ ወዳለ ደረጃ ማድረስ፤

ጥናታቸው የተጠናቀቀና የተረጋገጡ የጥናት ሰነዶች ወደግንባታ በማስገባት ተቋማት በተያዘላቸው ጊዜ እና በጀት እንዲጠናቀቁ ከተቃራጮች፤ከማህበረሰቡ፤ከመስኖ ተጠቃሚዎች ማህበርና ከአማካሪዎች ጋር አሰራርን በጠበቀ መልኩ የግንኙነት አግባብ ልማትን ያማከለ እንዲሆን ማድረግ፡፡

ግንባታቸው የጠጠናቀቁ የመስኖ ተቋት ተቋም እንዲሆኑና ራሳቸውን ችለው ልማቱን እንዲያካሂዱ የተጠናከረ የመስኖ ተጠቃሚዎች ማህበር በተቀመጠው አዋጅ፤ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲመሰረቱና የተመሰረቱት ደግሞ እንዲጠናከሩ የክትትልና ድጋፍ ሥራ ይሰራል፡፡

የቆላማ አካባቢዎች ልማት የአካባቢዎቹን ችግር በሚፈታ መልኩ ከሚመለከታቸው የክልልና የፌደራል ተቋማት ጋር በጋራ ዕቅድ የተመሰረተ የተግባርና የተግባቦት ሥራ ይሰራል፡፡

በተግባር እንቅስቃሴ የሚገኙ መልካም ልምዶችን እየቀመሩ ማስፋት፤ኪራይ ሰብሳቢነትን በመድፈቅ አገልጋይነትን ማሳደግ፣በቢሮው ያለው አመራርና ሙያተኛ ሥራውን በተደራጀ መልኩ በባለቤትነት እንዲመራ ማድረግ፣የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ተቋራጮችን፤አማካሪዎች እና ተጠቃሚዎችን በማገናኘትና በማወያየት የገጠሙ ችግሮችን መፍታት፤የተጠናከረ እና ዘመኑን የዋጀ የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት፡፡

በመስኖ ልማት ዘርፍ የተቋማዊ አቅምና የዘርፉን የሰው ሃብት ልማት ለማሳደግ አስቻይ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ መመሪያዎችና ስታንዳርድ ማዘጋጀት፤ተቋማዊ አሠራርን በማጠናከርና ፋሲሊቲዎችን ማሟላት፤በመስኖ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎችና የመስኖ ተጠቃሚዎችን አቅም መገንባት፤የመስኖ ልማትን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የሚያስተሳስር ሥርዓት መዘርጋት ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው:

## 9. የዕቅዱ ማስፈፀሚያ ሀብት

የቢሮውን ጠቅላላ በጀት የተቋቋመለትን ዓላማ ለመፈጸም በመመደብ ውጤታማ በሆነ መልኩ ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ የመስኖ አውታር ጥናትና ዲዛይን፤ ግንባታ፤ጥገናና ክትትልና

ግምገማ ተግባራትን ከብልሹ አሠራር በፀዳ መልኩ በወቅቱና በጥራት በመፈጸምና የንብረት አያያዝና አጠቃቀማችን በማሻሻል የመንግስት ሀብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል የሚደረግ ሲሆን የኦዲት አገልግሎት ሽፋንን በማሳደግ ወጪን ከብክነት በማዳን በ5 ዓመቱ ውስጥ ቢሮው ያቀዳቸውን ተግባራት ለማስፈጸም ብር 60,155,036,071.00 ሀብት ያስፈልጋል፤

| ተ.ቁ | የወጭ ርዕስ | የሚያስፈልግ በጀት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | የ5ዓመት ድምር |
| 1 | ለክልል ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ሥራ | 570,752,438.00 | 208,935,000.00 | 208,935,000.00 | 208,935,000.00 | 208,935,000.00 | 208,935,000.00 | 1,044,675,000.00 |
| | በፌደራል የተጀመሩ ከፍተኛ ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ሥራ ለማጠናቀቅ | | | | | | | 334,700,000.00 |
| 2 | ለክልል ፕሮጀክቶች ግንባታ ሥራ | 2,770,781,904.44 | 6,519,935,368.00 | 6,519,935,368.00 | 6,519,935,368.00 | 6,519,935,368.00 | 6,519,935,368.00 | 32,599,676,840.00 |
| | በፌደራል የተጀመሩ ከፍተኛ ፕሮጀክቶች ግንባታ ለማጠናቀቅ | | | | | | | 23,400,000,000.00 |
| 3 | ለተቋ/አስ/ጥገና ሥራ | 677,720,191.60 | 376,964,869.00 | 376,964,869.00 | 376,964,869.00 | 376,964,869.00 | 376,964,869.00 | 1,884,824,345.00 |
| 4 | ለፕሮጀክቶች ክትትል | 557,173,160.89 | 6,199,297.00 | 6,199,297.00 | 6,199,297.00 | 6,199,297.00 | 6,199,297.00 | 30,996,485.00 |
| 5 | ለልዩልዩ የአቅም ገንባታ ሥልጠና እና ግንዛቤ ፈጠራ | 6,587,900.00 | 9,121,250.00 | 9,121,250.00 | 9,121,250.00 | 9,121,250.00 | 9,121,250.00 | 45,606,250.00 |
| 6 | ለመደበኛ ደመወዝ | 30,269,673.00 | 31,783,157.00 | 33,372,315.00 | 35,040,930 | 35,040,930 | 35,040,930 | 170,278,262.00 |
| 7 | ለመደበኛ ሥራ ማስኬጃ | 92,274,152.00 | 106,115,275.00 | 122,032,566.00 | 134,235,822.00 | 140,947,613.00 | 140,947,613.00 | 644,278,889.00 |
| ድምር | | 4,705,559,419.93 | 7,259,054,216.00 | 7,276,560,665.00 | 7,290,432,536.00 | 7,297,144,327.00 | 7,297,144,327.00 | 60,155,036,071.00 |

## 10. ስጋቶችና እሳቤዎች

### ሀ. መልካም አጋጣሚ (እሳቤዎች)

መስኖ የአገሪቱ ዋና የምርት ማሳደጊያ በመሆኑ የፌደራሉና የክልሉ መንግስት ለመስኖ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ ትኩረት መስጠትና በጀት በመመደብ በርካታ የመስኖ ተጠቃሚ አርሶ አደሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ ሃብት በማፍራት ኑሯቸዉን ማሻሻል መቻላቸዉ አርሶ አደሩ በግንባታ ስራችን ላይ አወንታዊ ሚና እንዲኖራቸው ማድረጉ፤የመስኖ ልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጅዎች፣መመሪያ እና ደንቦች መኖር በግንባታ ስራዎቻችን ላይ ለሚያጋጥመን የመልካም አስተዳደር ችግር መፍተሄ ያስገኛል፤

የቴክኖሎጂ መስፋፋትና እድገት በግንባታ ስራዎች ወቅት ለመረጃ ልውውጥ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑ፤ትልልቅ የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክቶችን መገንባት እና ማማከር የሚችሉ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በክልላችን መኖራቸው፤አነስተኛ የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክቶችን መገንባት የሚችል በርካታ ልምድ ያላቸው እና አዲስ ወደ ስራ የሚገቡ ግንባታ ተቋራጭ ኢንተርፕራይዞች መፈጠራቸው፤ቁጥራቸው ያን ያህል ብዙ ባይባልመ በቂ ቁጥር ያላቸው የግል የመስኖ ግንባታ ተቋራጭ እና አማካሪ መኖራቸው፤ሰፊ የውሃ ህብት እና በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት ባለቤት መሆኑ በተጨማሪም በየደረጃው ያለ አመራር ስለመስኖ ያለው ግንዛቤ እያደገ በመምጠቱ ከክልል እስከ ወረዳ የተዘረጋው የፍትህ አደረጃጀት መኖሩ በጨረታ ወቅት እና በግንባታ ጊዜ ለሚገጥመን የፍትህ መጓደል ስርአት እያስከበሩ ለመስኖ ልማቱ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ

መጠነ ሰፊ የከርሰ ምድርና ገፀ ምድር የውሃ ሃብት ሰፊ የሚታረስና በመስኖ የሚለማ መሬት፤ የምእተ ዓመቱ የልማት ግቦች ተቀርጸው ተግባራዊ መሆናቸው፤የማሕበራዊ ተቋማት መስፋፋትና ለልማት ያላቸው ትኩረት እያደገ መምጣቱ የሚሉትና ሌሎች ብዙ ጉዳዮች የመስኖ ሥራን ለማፋጠን ጉልህ ሚናያላቸው እሳቤዎች ሁነው ተለይተዋል፡፡

### ለ. ስጋቶች

የመገንባት አቅም ውሱንነት መኖር፣ የግል ተቋራጭ እና ኢንተርፕራይዞች የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና አማካሪዎች የመስኖ ፕሮጀክቶችን ጥናትና ዲዛይንና ግንባታ የመሥራት

ኃላፊነት ቢሰጣቸውም ያሉበት ነባራዊ ሁኔታ የመንግስትንና የህዝብን ፍላጎት እና እርካታ የሚያመጣ ባለመሆኑ ለብዙ አመታት በማቆየት ክልሉ ለተጨማሪ ወጭ መጋለጡና የክልሉ ህዝብ ከመስኖ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም በወቅቱ እናዳያገኝ ያደርገዋል፣ የተመደበልንን በጀት ሳንጠቀም እንድንመለስ ያደርጋል፤

አዲስ ኢንተርፕራይዞች በበቂ ሁኔታና ሥራው በሚጠይቀው ሙያ ያለመደራጀት ችግር ሊያጋጥም እና የተሰጣቸውን ግንባታም የመፈጸም አቅማቸው አናሳ ሆኖ ሊገኝ ይችላል በተጨማሪም ተቋራጮች አሸንፈው ወደስራ ከገቡ በኂላ የዋጋ ይሻሻልልኝ ጥያቄ እያደገ መምጣት በግንባታ ሥርችን ቅልጥፍና ላይ ሚናው የጎላ ነው፤የንግዱ ማህበረሰብ በአቋራጭ የመበልጸግ ዝንባሌ በአስተሳሰብም ሆነ በተግባር መኖር እንዲሁም የተቋሙ አመራርና ባለሙያ በተመሳሳይ የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባር ሊያጋጥም ስለሚችል ከፍተኛ የክትትል ሥራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

ወቅቱን ባልጠበቀ ዝናብ ምክንያት በሚፈጠር የጎርፍ ፍሰት በግንባታ ሂደቶች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚሳድር መሆኑ፤ ሰብል በወቅቱ አለመስብሰብ፤የመሰረት ልማት አለመስፋፋት እንዲሁም በመስኖ ልማት ላይ ያለ የግንዛቤና የአስተሳሰብ ችግር ባለመሬቶች ከወሰን ማስከበር ጋር ተያይዞ መሰናክል መሆን እና መሬትን ክሶስተኛ ወገን ነፃ መድረግ አለመቻል፤

የወቅቱ የገበያ አለመረጋጋት፤የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት ከመኖር ጋር ተያይዞ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ የማይጠናቀቁ ከሆነ የዋጋ ንረቱ የፕሮጀክቱን አጠቃላይ ወጪ ከፍተኛ ያደርገዋል፤የግንባታ ግበዓት እጥረት በተለይም ስሚንቶ በገበያ ላይ አለመገኘት እንዲሁም ከፍተኛ የዋጋ ንረት (ስሚንቶ፣ ነዳጅ እና ብረት) ፤እና የኤሌክትሮ መካኒካል አቅርቦት እጥረት( ጠላቂ ፓምፕ፤ጀነሬተሮች እና አክሰሰሪዎች)፤

በክልላችን የገጠመን በጸጥታ ምክንያት የመንገድ መዘጋት እንቅስቃሴ መታወክ ችግሮች ከገጠመን፤ በየደረጃዉ ያለዉ አመራር በቂ ግንዛቤ አለመያዝ ትኩረትም ያለመስጠት የመስኖ ተቋማትን ለመገንባትና ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ችግር ይሆናል፡፡

ለመስኖ ስራ በቂ በጀት ያለመመድብና በጀት በወቅቱ ያለመለቀቅ ችግር ሊያጋጥም ይችላል፤

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት ሥጋቶች የማይገጥሙን ከሆነ ክልሉ ያሉትን ጸጋዎችና መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀም በመስኖ ልማቱ ሊገኝ የሚችለው ትሩፋት መጠነ ሰፊ ሁኖ የክልሉ ህዝብ በቤተሰብና በክልል ደረጃ የምግብ ዋስትናውና ሉዓላዊነቱ ተረጋግጦ ከሀገር ውስጥ ፍጆታ በላይ በማምረት ወደ ውጭ እክስፖርት በማድረግ በግብርና ልማቱ ዘርፍ በዓመት እስከ ሦስት ጊዜ እንዲመረት በማድረግ ረገድ የመስኖ ልማቱ የአንበሳውን ድርሻ ይወጣል፡፡

## 11. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

ከፍተኛ እና መካከለኛ የፌደራል መስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታና አስተዳደር በፌደራል መንግስትና በክልሉ ከፍተኛ አመራር በተቀመጠው አደረጃጀትና አሰራር መሰረት እየተገመገሙ ይመራሉ፡፡

በክልል የሚፈጸሙ ፕሮጀክቶች ጠቅላላ እንቅስቃሴ በሁሉም ደረጃ ባሉ አመራርና ባለሙያዎች ክትትልና ግምገማ ይካሄዳል፤ የመስክ ሪፖርት እየቀረበ የተገኘው ግኝት በማኔጅመንት ይገመገማል፤ በተጨማሪ አግባብ ካላቸው የስራ ሂደቶች የተውጣጣ የባለሙያዎች ቡድን በተመረጡ ዞኖችና ወረዳዎች የመስክ ክትትል እገዛና የስራ ግምገማ ይካሄዳል፤የቢሮው ማኔጅመንት በተመረጡና አስተማሪ ሊሆኑ በሚችሉ ፕሮጀክቶች ዞኖችና ወረዳዎች በመገኘት የስራ ግምግማ ይካሄዳል፤ ጠንካራ ተሞክሮዎችን ቀምሮ ለቢሮው ስራ በግብዓትነት እንዲያገለግል ይደርጋል፤

ከህዝብ ክንፉ ጋር እየተገናኙ ሥራዎችን በመገምገም ችግሮች ለመፍታት የቢሮው ማኔጅመንት በዞኖች እየተገኙ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤ በአመት አንድ ጊዜ የመስኖ ተቋማት ቆጠራ ማካሄድና ወደ መረጃ ቋት ማስገባት፤በግምገማው የተገኙ ክፍተቶችና ያልተከናወኑ ተግባራት እየተለዩ በቀጣይ እንዲፈጸሙ የአፈጻጸም አቅጣጫ ይቀመጣል፤ በዓመት አንድ ጊዜ የተገልጋዮች እርካታ ዳሰሳዊ ጥናት ይደረጋል፡፡

ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል የተጠቃለለ ሪፖርት በማጠናከር በተቀመጠው አሰራር መሰረት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት በማዘጋጀት ይቀርባል፤ የተሰሩ ሥራዎችን የሚዲያና የተግባቦት ሥራ ይሰራል፤

## 12. የድርጊት መርሀ-ግብር

| ተ.ቁ | የተቋሙ ዝርዝር ተግባራት | መለኪያ | እስከ 2017 አፈጻጸም መነሻ | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጥናትና ዲዛይን የሚሰራላቸው ፕሮጀክቶች | በቁጥር | 794 | 122 | 122 | 122 | 122 | 127 |
| | ጥናትና ዲዛይን በሚሰራላቸው የሚለማ መሬትፕሮጀክቶች | በሄ/ር | 146,850 | 38,930 | 38,930 | 38,930 | 38,930 | 221,930 |
| | ጥናትና ዲዛይን በሚሰራላቸው ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ ብዛት በቁጥር | ወ | 41,007 | 10,900 | 10,900 | 10,900 | 10,900 | 62,140 |
| | | ሴ | 10,252 | 2,725 | 2,725 | 2,725 | 2,725 | 15,535 |
| | | ድ | 51,259 | 13,626 | 13,626 | 13,626 | 13,626 | 77,676 |
| 1.1 | የአነስተኛ መስኖ ብዛት | በቁጥር | 569 | 118 | 118 | 118 | 118 | 118 |
| | የአነስተኛ መስኖ ስፋት | በሄ/ር | 65,975 | 13,630 | 13,630 | 13,630 | 13,630 | 13,630 |
| 1.2 | የመካከለኛ መስኖ ብዛት | በቁጥር | 224 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| | የመካከለኛ መስኖ ስፋት | በሄ/ር | 74,875 | 6,560 | 6,560 | 6,560 | 6,560 | 6,560 |
| 1.3 | ጥናትና ዲዛይን የሚሰራላቸው ከፍተኛ ፕሮጀክቶች | በቁጥር | 1 | | | | | 5 |
| | ጥናትና ዲዛይን የሚሰራላቸው ከፍተኛ ፕሮጀክቶች የሚለማ መሬት | በሄ/ር | 6,000 | | | | | 183,000 |
| 3 | ግንባታ የሚሰራላቸውን ፕሮጀክቶች | በቁጥር | 6,148 | 320 | 320 | 320 | 320 | 320 |
| | በሚገነቡ ፕሮጀክቶች የሚለማ መሬት | በሄ/ር | 260,269 | 32,020 | 32,020 | 32,020 | 32,020 | 32,020 |
| | በሚገነቡ ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ ብዛት በቁጥር | ወ | 74,555 | 8,967 | 8,967 | 8,967 | 8,967 | 15,214 |
| | | ሴ | 18,639 | 2,241 | 2,241 | 2,241 | 2,241 | 3,803 |
| | | ድ | 93,194 | 11,207 | 11,207 | 11,207 | 11,207 | 19,016 |
| 2.1 | የአነስተኛ መስኖ ብዛት | በቁጥር | 4,609 | 240 | 240 | 240 | 240 | 240 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የአነስተኛ መስኖ ስፋት | በሄ/ር | 175,869 | 22,970 | 22,970 | 22,970 | 22,970 | 22,970 |
| 2.2 | የመካከለኛ መስኖ ብዛት | በቁጥር | 1,539 | 80 | 80 | 80 | 80 | 80 |
| | የመካከለኛ መስኖ ስፋት | በሄ/ር | 84,401 | 7,660 | 7,660 | 7,660 | 7,660 | 7,660 |
| 3 | በፌደራል ግንባታ የሚሰራላቸው ከፍተኛ ፕሮጀክቶች | በቁጥር | 1 | | | | | 6 |
| | በፌደራል ግንባታ የሚሰራላቸው ከፍተኛ ፕሮጀክቶች የሚለማ መሬት | በሄ/ር | 5,604 | | | | | 50,578 |
| 4 | የተቋቋሙ የመ/ው/ተጠቃ/ማህበር | በቁጥር | 1,600 | 320 | 320 | 320 | 320 | 320 |
| 5 | የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን (motor pump) ማሰራጨት | በቁጥር | 14,845 | 1,500 | 1,500 | 1,300 | 1,200 | 1,000 |
| | በተሻሻሉ ቴክኖሎጅዎች የሚለማ መሬት | በሄ/ር | 51,958 | 675 | 675 | 675 | 675 | 675 |
| | የተሻሻሉ የመስኖ ውኃ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም | በቁጥር | 14 | 1 | 2 | 3 | 5 | 6 |
| | የተሻሻሉ የመስኖ ውኃ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች የሚለማ መሬት | በሄ/ር | 516 | 37 | 74 | 111 | 185 | 222 |
| 6 | የሚጠገኑ የመስኖ ተቋማት | በቁጥር | 119 | 90 | 89 | 88 | 85 | 80 |
| 7 | የተከናወነ የቆላማ አካባቢዎችን ሁሉን አቀፍ ልማት አፈጻጸም | በ% | 0 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 |
| 8 | የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠትና ግንዛቤ ፈጠራ መስራት | በቁጥር | 892 | 1,525 | 1,525 | 1,525 | 1,525 | 1,525 |
| 9 | የተፈጠረ የሥራ ዕድል | በቁጥር | 45,000 | 46,000 | 47,000 | 48,000 | 49,000 | 50,000 |